ዐቂደቱል ሙስሊም

አንደኛ ደረጃ - ሁለተኛ ደረጃ - ሦስተኛ ደረጃ

አዘጋጅ ፦ አቡ አብድረህማን አብደላህ ኢብኑ አህመድ አልኢርያኒ

ተርጓሚ ፦ አቡ አብድልመናን ኻሊድ ኢብኑ ጠይብ

ማውጫ

አንደኛ ደረጃ

ገፅ

ጌታህ ማነው ……..

ሐይማኖትህ ምንድነው ……..

ነብይህ ማነው …….

ማነው የፈጠረክ …….

አላህ እኛን የፈጠረው ለምንድነው ……

በአላህ ባሮች (በሰው ልጆች) ላይ በመጀመሪያ ግዴታ የሆነው ነገር ምንድነው ……

የላኢላሃኢለላህ ትርጉም ምንድነው ……..

መሐመድ (صلى الله عليه وسلم) የአላህ መልክተኛ ናቸው ማለት ምን ማለት ነው ……

አላህ በሰዎች ላይ ያለው መብት ምንድነው ……..

ሰዎች በአላህ ላይ ያላቸው መብት ምንድነው ……..

የእስልምና መሠረቶች ስንት ናቸው ……

የኢማን መሠረቶች ስንት ናቸው .....

የኢህሳን መሠረቶች ስንት ናቸው .....

አላህ ያለው የት ነው .....

አላህ ከኛ ጋር ነውን .....

የወልይ ትርጉም ምንድነው .....

ከፍጥረታት ውስጥ መልካም ሰሰዎች እነማን ናቸው ከፉዎቹስ እነማን ናቸው .....

ከወንጀሎች ሁሉ ከባድ ምንድነው .....

ወደ ምድር የተላከው የመጀመሪያው ረሱል ማነው ..

የመጨረሻው ረሱል ማነው.....

ሁለተኛ ደረጃ

የዲን ደረጃዎች ስንት ናቸው.....

ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው .....

ኢማን ማለት ምን ማለት ነው .....

ኢህሳን ማለት ምን ማለት ነው .....

ዒባዳ አላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው መስፈርቱ መንድነው

የአላህ መልክተኞች በአጠቃላይ ዳዕዋ ያደረጉት ወደምንድነው

ዒባዳ ማለት ምን ማለት ነው ……..

ዒባዳ በስንት ይከፈላል ……

ቢድዓ ምንድነው ……..

የቢድዓ ሁክም (ፍርድ) ምንድነው ……

ከባዱ በደል ምንድነው ……

ተውሂድ ማለት ምን ማለት ነው ……..

ተውሂድ በስንት ይከፈላል ……

ተውሒድ አርሩቡቡያ ትርጉሙ ምንድነው ……..

ተውሒድ አልኡሉሂያ ትርጉሙ ምንድነው ……..

ተውሒድ አልአስማኢ ወሲፋት ትርጉሙ ምንድነው

ሦስተኛ ደረጃ

በአላህ ማመን ……..

በመላእክት ማመን ……..

በመፃህፍት ማመን ……

በመልእክተኞች ማመን .....

በመጨረሻው ቀን ማመን .....

በቀደር ማመን .....

የላኢላሃኢለላህ መሠረቶች .....

የላኢላሃኢለላህ መስፈርቶች .....

1. እውቀት .....
2. እርግጠኛነት .....
3. ኢኽላስ .....
4. እውነተኛነት .....
5. ውዴታ .....
6. መጎተት .....
7. መቀበል .....
8. በጣዖት መካድ .....

እስልምናን የሚያበላሹ ነገሮች .....

የተወሰኑ ክፍሎች .....

ተፈቃጅ የሆኑት የተወሱል ዓይነቶች .....

ክልክል የሆኑት የተወሱል ዓይነቶች .....

. ቢድዓ የሆነ ተወሱል .....

. ሽርክ የሆነ ተወሱል .....

በነብያችን (صلى الله عليه وسلم) ተወሱል የማድረግ ፍርድ

በርሳቸው በማመን እርሳቸውን በመውደድና በመከተል ተወሱል ማድረግ

በርሳቸው ዱዓ ተወሱል ማድረግ .....

በክብራቸው ተወሱል ማድረግ

የቀብር ዚያራ (ጉብኝት) ክፍሎች .....

ሸሪዓዊ (የተፈቀደ) ዚያራ .....

ቢድዓ (መጤ) የሆነ የዚያራ ዓይነት .....

ሽርክ ያለበት ዚያራ .....

በረካን ከቦታዎች ወይም ከፋናዎች እንዲሁም ሙትም ይሁኑ ሕያው
ከሆኑ ሰዎች መፈለግ .....

የተርጓሚው መቅድም

አልሐምዱሊላሂ ምስጋና ተገባው

ሀያል አሸናፊ ብቸኛ ለሆነው

ለጌታችን አላህ ለዛ ለማይሞተው

ከፍጡራን በላይ ሰማይ ለሚገኘው

ከጨለማ አውጥቶ ብርሀኑን ለሠጠኝ

ከክህደት ጠብቆ ሙስሊም ላደረገኝ

በሕይወት እያለው ነበርኩኮ መይት

ከውልደት በኋላ አስራ ስምንት ዓመት

ከዛ በኋላ ነው አላህን ያወቅኩት

የዲን ሰው አድርጎ ሠጠኝ አዲስ ህይወት

በጣም በጭር ጊዜ ቀርአንን ለገስከኝ

የዓሊሞች መንደር ወስደህ ደባለቅከኝ

ሒፍዙንም ጨምረህ ሱናን አሳወቅከኝ

ያንተ እገዛ እንጂ መች አቅም ነበረኝ

አንተ ደበቅክልኝ ነውሬን ጉድለቴን

ሰው እንዳያውቅብኝ የውስጥ ችግሬን

የውስጤን ሚስጥሮች ሳሊሆች ቢያውቁት

ይጠሉ ነበረ ሰላምታ ለመስጠት

ብዙ ፀጋዎችን አጎናፅፈኸኛል

ቆጥሬ ልዘልቀው በጣም ይከብደኛል

መሥጋናዎች ሁሉ ላንተ ይገባህል

በልብና ምላስ እዲሁም በአካል

ሰላትና ሰላም በነብያችን ላይ

በቤተሰባቸው በሰሀቦችም ላይ

በተከተላቸው ዛታቸውን ሳያይ

ይውረድ ከጌታችን ከሚገኘው ሰማይ

ከዚህ በመቀጠል እኔ ማስቀምጠው

ከሁሉ ቀዳሚው ተውሒድ መሆኑን ነው

ለዚህ አባባሌ ትልቁ መስረጃው

ሁሉንም ሩሱሎች አላህ ሲልካቸው

ቀድመው ሚያስተምሩት ለሁሉም ህዝባቸው

አላህን አንድ አርጉ እርሱን ተገዙ ነው

ሽርክን ተጠንቀቁ ውጤቱ ሸር ነው

ነብዩም ሙዓዝን ለዳዕዋ ሲልኩት

ወደ የመን ሀገር እንዲህ ብለው ሸኙት

ትሄዳለህና አህለል ኪታቦች ጋር

መጀመሪያ ቀድመህ ተውሒድን አስተምር

አስርዕ በውስጣቸው ያንድነቱን ሚስጥር

እኔም ይሄን ይገፍ ተነሳው ቆርጬ

ተውሒድን ላስተምር ከሁሉ አብልጬ

አቂደቱል ሙስሊም ኪታብ አገኘውኝ

መተርጎም ልጀምር ብዕር አነሳውኝ

ፍቃዱን ጠየኩት ያዘጋጀው ሸይን

የመን ሚገኘውን አብደላ ኢርያንን

መፍቀዱን ነገረኝ አላህ ይጠብቀው

ኸይር ጀዛውንም በጀነት ይክፈለው

እኔንም እርሱንም እንዲሁም አንባቢን

በብዙ በጥቂት የተባበረኝን

በዚች ትንሽ መፅሐፍ በያዘች ተውሒድን

ተጠቃሚ ያርገን መሀሪው ጌታችን

ይህንን መፅሐፌን ሁሌ ስታነቡት

ዱዓ አድርጉልኝ ይህንን በማለት

ያ አላህ ለካሊድ አንተ እዘንለት

ከወንጀልም አጥራው የቂያማ ዕለት

በሰለፍያ ላይ ፅናትንም ስጠው

ወንጀልና ስሜት እንዳያሳስተው

አማፀነዋለው አዛኙ ጌታዬን

ብሩክ እንዲያደርግ ተከታዩ ዘራን

እንዲምርልኝም ሁሉንም ወንጀሌን

የወለዱኝንም የኡሚና የአቢን

የወንድም የሴትም የሁሉም ሙእሚንን

እርሱ ቻይ ነውና ይቀበለኝ አሚን

ሁሌ ወደ አላህ ከጃይና ፈላጊ የሆነው

ሻሊድ ጠይብ

የአዘጋጁ መቅድም

ለዓለማቱ ጌታ አላህ ምስጋናው የተገባው ነው መሐመድም (صلى الله عليه وسلم) የአላህ ባርያና መልክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለው። ከዚህ በመቀጠል፡-

ንፁህ የሆነ ተውሒድና ትክክለኛ የሆነ ዓቂዳ አሳሳቢ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛና ግዴታነታቸውም የበረታ ነው ምክንያቱም ለምንሰራው ማንኛውም ዒባዳ ትክክለኛነትና አላህም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው መስፈርቶች ናቸውና ለዚህም ነው የነብያት ተከታዮች ይህንን ወሳኝ ነጥብ የሚቃረንንና ጥራቱንም የሚቀንስን ጉዳይ ላቅ ያለ ትኩረት የሰጡት። እንዲሁም የዚህ ኡማ ትክክለኛ ዑለማዎች በማስተማርና መፅሀፍትን በማዘጋጀት ከሚያደርጉት ትግልና ጥረት ወስጥ ከፍተኛውን ጊዜ ለዚህ ርዕስ ሰጥተውታል። ይህም በመሆኑ በዓቂዳ ዙሪያ የተፃፉ መፅሐፍቶች በእስላማዊ መፅሐፍት ቤቶች ውስጥ ከሌሎች ርዕሶች በበለጠ ሰፊ ድርሻንና ቀዳሚነትን ይዘዋል።

በዚህ አጭር ዑሁፍ ውስጥ ከእስልምና ዑለማዎች መፅሐፍት የተወሰዱ ቀላልና ጥቅማቸውና ውጤታቸው ግን የጎላ ትምህርቶች የተካተቱ ሲሆን በሦስት ደረጃዎች ከፍያቸዋለው።

አዘጋጁን እንዲሁም አንባቢያንን በዚህ መፅሐፍ ተጠቃሚ እንዲያደርገን አላህን እማፀነዋለው !!!

አዘጋጁ

አንደኛ ደረጃ

1. **ጌታህ ማነው? ከተባልክ**

ጌታዬ እንዲሁም የዓለማት ጌታ አላህ ነው በል።

ማስረጃውም አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴾

((ለዓለማቱ ጌታ አላህ ምስጋና የተገባ ነው)) (አል ፋቲሀ 2)

2. **ሐይማኖትህ ምንድነው? ከተባልክ**

ሐይማኖቴ ኢስላም ነው በል።

ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱلدِّينَ عِندَ ٱللَّهِ ٱلۡإِسۡلَٰمُ ﴾

((አላህ ዘንድ(የተደደ) ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው))

(አል ኢምራን 19)

3. **ነብይህ ማነው ? ከተባልክ**[1]

ነብዬ መሐመድ(صلى الله عليه وسلم) **ነው በል ማስረጃውም የአላህ ንግግር ነው፡-**

﴿ مُّحَمَّدٌ رَّسُولُ ٱللَّهِ ﴾

((መሐመድ የአላህ መልክተኛ ነው)) (ፈትህ 29)

4. **ማነው የፈጠረክ? ከተባልክ** [1]

እኔን የፈጠረኝ አላህ ነው እርሱ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው በል አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱللَّهُ خَٰلِقُ كُلِّ شَيۡءٖ ﴾

((አላህ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው)) (ዙመር 62)

5. **አላህ እኛን የፈጠረን ለምንድነው? ከተባልክ**

---

(1) እነዚህ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሶስት ያሉት ጥያቄዎች ማንኛውም ሰው ቀብር እንደገባ በመጀመሪያ የሚጠየቃቸው ጥያቄዎች መሆናቸውን ነብያችን በሐዲሳቸው ነግረውናል

አላህ የፈጠረን እርሱን እንድንገዛው ነው በል
ማስረጃውም አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ٥٦ ﴾

ጂኒንም ይሁን ሰውን (እኔን) ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም)) (አዝዛሪያት 56)

6. በአላህ ባሮች (በሰው ልጆች) ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ግዴታ የሆነው ነገር ምንድነው? ከተባልክ

የአላህን አንድነት (ተውሂድ) መማር ነው [2] በል_ለዚህም ማስረጃ የአላህ መልእክተኛ (صلى الله عليه وسلم) ሙዓዝን (ለዳዕዋ) ወደ የመን በላኩት ጊዜ የተናገሩት ይህ ንግግር ነው፡፡

---

(2) ምክንያቱም አንድ ሰው ዒባዳው አላህ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው አላህን በብቸኝነት ከተገዛ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ነው ሁሉም የአላህ መልእክተኞች አላህ ወደ ህዝቦቻቸው ሲልካቸው የመጀመሪያ ጥሪያቸው አላህን በብቸኝነት እንዲገዙና ከሽርክ እንዲርቁ ነው፡፡ ስለ ተውሒድና ዐቂዳ ሰፊ ጊዜና ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር ሙስሊሞችን ይከፋፍላል ብሎ ማመን መጤ(ቢድዓ) የሆነ ውድቅ አስተሳሰብ እንጂ የአላህ መልእክተኞች መንገድ በጭራሽ አይደለም፡፡

إِنَّكَ تَقْدَمُ عَلَى قَوْمٍ أَهْلِ كِتَابٍ فَلْيَكُنْ أَوَّلَ مَا تَدْعُوهُمْ

إِلَيْ أَنْ يُوَحَّد اللَّه

((አንተ ወደ መፅሐፍ ባልተቤቶች ትሔዳለህና የመጀመሪያ ጥሪህ አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ ይሁን)) (ቡኻሪ 6824 ሙስሊም 28 ከኢብኑ ዐባስ

7. የላኢላሃኢለላህ ትርጉም ምንድነው? ከተባልክ

ትርጉሙ ከአላህ በስተቀር <u>በእውነት</u>[3] የሚመለክ አምላክ የለም ማለት ነው:: በል ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

---

(3) የተሳሳቱ የላኢላሃኢለላህ ትርጉሞች አሉ ለምሳሌ ብዙ ሙስሊሞች የለመዱት ትርጉም (**ከአላህ በስተቀር የሚመለክ የለም**) የሚለውን ነው ይህ ደግሞ ስህተት ነው ምክንያቱም ከአላህ ውጭ የሚመለኩ ብዙ ነገሮች በተጨባጭ ይስተዋላሉና ለመጥቀስ ያህል ድንጋይንና ዛፍን የሚያመልክ አለ የሳሊህ ሰዎችን ቀብር የሚያመልክ አለ መላይካዎችንና ነብያቶችን የሚያመልክ አለ... ነገር ግን እነዚህ ሁሉ የሚመለኩት በውሸት ነው ምክንያቱም አምልኮት አይገባቸውም፡፡ በብቸኝነት አምልኮት የሚገባው አላህ ብቻ ነው ስለዚህ የላኢላሃኢለላህን ቃል ስንተረጉም **<u>በእውነት</u>** የሚለውን ቃል ስንጨምርና (**ከአላህ በስተቀር <u>በእውነት</u> የሚመለክ የለም**)

﴿ ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡحَقُّ ﴾

((ይህ አላህ እርሱ እውነት በመሆኑ ነው...)) (ሉቅማን 30)

8. **መሐመድ (صلى الله عليه وسلم) የአላህ መልክተኛ ነው ማለት ምን ማለት ነው?** ከተባልክ

ትርጉሙ እርሱን መከተልና መታዘዝ ግዴታ የሆነና አጠቃላይ ወደ ሰው ልጆች የተላከ የአላህ መልክተኛ ነው[4] ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

---

ስንል ከአላህ ውጭ የሚመለኩት ሁሉ በውሸት መሆኑን ግልፅ ያደርግልናል፡፡

(4) አንድ ሰው በመሐመድ (صلى الله عليه وسلم) መልክተኝት አምኖለው ካለ አራት ነገሮችን ማሟላት አለበት፡-

1. እርሳቸው ያዘዙትን ሁሉ መታዘዝ
2. የተናገሩትን በሙሉ እውነት ብሎ መቀበል
3. የከለከሉትን ነገር ሙሉ በሙሉ መከልከል

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا كَآفَّةٗ لِّلنَّاسِ ﴾

((አንተን ለሰዎች ሁሉ አጠቃላይ ቢሆን እንጂ አላክንህም))

(ሰበአ 28

በሌላም አንቀፅ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمۡ عَنۡهُ فَٱنتَهُواْ ﴾

((መልክተኛውም የሰጣችሁን (ሁሉን) ነገር ያዙት ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ)) *(አል ሐሸር 7)*

9. አላህ በባሮቹ ላይ ያለው መብት ምንድን ነው? ከተባልክ

አላህ በባሮቹ ላይ ያለው መብት እርሱን ብቻ ሊያመልኩና በርሱም ላይ ምንንም ሀይል ላያጋሩ ነው በል

---

4. አላህን ሲገዛ (ዒባዳ ሲስራ) እርሳቸው ባሳዩትና ባስተማሩት መልኩ ብቻ መሆን አለበት ይህ ካልሆነ ስራው ቢድዐ ይሆንበታል።

10. ሰዎች በአላህ ላይ ያላቸው መብት ምንድን ነው?ከተባልክ

እነርሱ በርሱ ላይ ሌላን አካል እስካላጋሩ ድረስ ላይቀጣቸው ነው በል[5] ። ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡትና ሙዐዝ አብኑ ጀበል ያስተላለፈው ሐዲስ ለነዚህ ሁለት ጥያቄዎች መልስ ማስረጃ ይሆናል የአላህ መልክተኛ (صلى الله عليه وسلم) እንዲህ ይላሉ፡-

---

(5) ይህ የሰው ልጆች በአላህ ላይ ያላቸው መብት አላህ በእዝነቱና በችሮታው በራሱ ላይ ፈቅዶ ያደረገው እንጂ አላህ ተገዶ አይደለም ፍጡር ከፍጡር ጋር ካለው መብት ጋር በፍፁም አይመሳሰልም አላህ በሚሰራው ነገር ላይ አይጠየቅምና

አላህ እንዲህ ይላል ፡-

﴿ لَا يُسْـَٔلُ عَمَّا يَفْعَلُ وَهُمْ يُسْـَٔلُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾

(((አላህ)በሚሰራው ሁሉ ኣይጠየቅም እነርሱ (ፍጥረቶቹ) ግን ይጠየቃሉ))

(አል አንቢያ 23)

« فَإِنَّ حَقَّ اللَّهِ عَلَى الْعِبَادِ أَنْ يَعْبُدُوا اللَّهَ وَلاَ يُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا وَحَقُّ الْعِبَادِ عَلَى اللَّهِ عَزَّ وَجَلَّ أَنْ لاَ يُعَذِّبَ مَنْ لاَ يُشْرِكُ بِهِ شَيْئًا)) »

((አላህ በባሮቹ ላይ ያለው መብት እርሱን ብቻ ሊያመልኩና በርሱም ላይ ምንንም ኃይል ላያሻርኩ ነው፤ ሰዎች በአላህ ላይ ያላቸው መብት ደግሞ በርሱ ላይ ሌላን ኃይል ከማሻረክ ወንጀል የፀዱ እስከሆኑ ድረስ ላይቀጣቸው ነው።))

11 .የእስልምና መሰረቶች (አርካኑል ኢስላም) ስንት ናቸው? ከተባልክ

አርካኑል ኢስላም አምስት ናቸው በል እነርሱም፡-

1. ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም ሙሀመድም የአላህ መልክተኛ ነው ብሎ መመስከር
2. ሰላትን መስገድ
3. ዘካ መስጠት
4. የረመዳንን ወር ፆም መፆም
5. አቅሙ በቻለ ሰው ላይ ሀጅን ማድረግ

ለዚህም ማስረጃ ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡትና
አብደላ ኢብኑ ዑመር ያስተላለፉት የአላህ መልክተኛ
(صلى الله عليه وسلم) ሐዲስ ነው እንዲህ አሉ፡-

« بُنِىَ الإِسْلاَمُ عَلَى خَمْسٍ شَهَادَةِ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ وَإِقَامِ الصَّلاَةِ وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ وَحَجِّ الْبَيْتِ وَصَوْمِ رَمَضَانَ ».

((እስልምና በአምስት ነገሮች ላይ ተገንብቷል፤ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም መሐመድም የአላህ መልክተኛ ነው ብሎ መመስከር፣ ሰላትን መስገድ፣ ዘካን መስጠት፣ ረመዳንን መፆም፣ ሀጅን ማድረግ))

12. የእምነት መሰረቶች (አርካኑል ኢማን) ስንት ናቸው? ከተባልክ

አርካኑል ኢማን ስድስት ናቸው በል እነሱም፡-

1. በአላህ ማመን
2. በመላእክቶች ማመን
3. በመፃህፍቶች ማመን
4. በመልክተኞች ማመን

5. በመጨረሻው ቀን ማመን

6. በጥሩውም በመጥፎውም የአላህ ውሳኔ ማመን

ለዚህም ማስረጃ የአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) ጅብሪል ስለኢማን ለጠየቃቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ነው እንዲህ አሉ፡-

أَنْ تُؤْمِنَ بِاللَّهِ وَمَلاَئِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ وَالْيَوْمِ الآخِرِ وَتُؤْمِنَ ((

بِالْقَدَرِ خَيْرِهِ وَشَرِّهِ

((ኢማን ማለት፡- በአላህ፣ በመላእክቶቹ፣ በመፃህፍቶቹ በመልክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና በጥሩም ይሁን በመጥፎው የአላህ ውሳኔ ማመን ነው))

13. የኢህሳን መሰረቶች (አርካኑል ኢህሳን) ስንት ናቸው?

ከተባልክ

የኢህሳን መሰረት አንድ ነው በል እሱም ፡-

አላህን እደምታየው ሆነህ ልታመልከው ነው አንተ እንደምታየው ካልሆንክ እርሱ ያይሀልና ማስረጃውም *ሙስሊም በዘገበውና ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ባስተላለፉት*

ሐዲስ የአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) ለጂብሪል መልስ ሲሰጡ እንዲህ አሉ፡-

((أَنْ تَعْبُدَ اللَّهَ كَأَنَّكَ تَرَاهُ فَإِنْ لَمْ تَكُنْ تَرَاهُ فَإِنَّهُ يَرَاكَ))

((ኢህሳን አላህን እንደምታየው ሆነህ ልትገዛው ነው አንተ እንደምታየው ካልሆንክ እርሱ ያይሀል))

14. አላህ የት ነው ያለው? ከተባልክ

አላህ ከአርሹ ላይ ከፍ ብሎሰማይ ነው ያለው በል[6]::

ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

---

(6) አላህን ከፍጡራን ባህሪ ጋር አናመሳስልም በሚል ሙገታ አላህ ከዐርሽ በላይ አይደለም በማለት የሚያስተባብሉ ሰዎች አሉ እነዚህ ሰዎች **አሻዒራ** በመባል ይታወቃሉ::የዚህ ቡድን መስራች የነበረው **አቡልሀሰን አል አሸዓሪይ** ይህንን የጥመት ጎዳና በመተው ቀርኣንና ሀዲስን በሰሐቦች ግንዛቤ ተገንዝቦ መንገዘን መርሁ ወዳደረገው የአህለሱና መንገድ ተመለሷል:: ለዚህም ማስረጃ መጨረሻ አካባቢ የፃፈው **(ኢባና)** የሚባለው ኪታቡ በቂ ነው::ነገር ግን ሙስሊሞችን ለማጥመም ቆርጠው የተነሱ ሰዎች የርሱ ተከታይ ነን በማለትና ራሳቸውን አሻዒራ ብለው በመሰየም አሁን ድረስ ሙስሊሞችን ከዚህ ተፈጥሮአዊ ዐቂዳቸው ለማውጣት ደፋ ቀና እያሉ ይገኛሉ:: አላህ ከነዚህ ሰዎች ተንኮልና ጥመት ይጠብቀን፤፤፤ ***ግን እነዚህ ሰዎች አላህ ከዐርሽ በላይ አይደለም የሚሉት ለምንድነው?***

ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡ እንዲህ አሉ ፡- ‹‹**አላህ ከዐርሽ በላይ ነው ካልን አላህ ከዐርሽ ፈላጊ ነው ማለትን ያስይዛል ከነገራቶች መፈለግ ደግሞ የፍጡር ባህሪ ነውና ይህንን ባህሪ ለአላህ አናፀድቅም**›› አኛ ደግሞ ለዚህ ንግግራቸው ይህንን መልስ እንሰጣቸዋለን ፡- **አላህ በቁርኣኑ ‹‹እኔ ከዓለማት የተብቃቃው ነኝ››**ከማንም ፈላጊ አይደለውም ከማለቱ ጋር ‹‹**እኔ ያለሁት ከዐርሽ በላይ ነው**›› አለ፡፡ ምክንያቱም ‹‹**ኢስተዋ**››የሚለው የአረብኛ ቃል ትርጉም በዓረብኛ ‹**ዓላ**› ‹**ኢርተፈዐ**› ‹**ሰዒደ**› ሲሆን ይህንን ቃል ወደ አማርኛ ፍቺ ስንመልሰው ‹‹**ከፍ አለ**›› የሚል ትርጉምን ይሰጠናል፡፡ በመሆኑም አላህ ከዐርሽ በላይ ነኝ ማለቱ ከዐርሽ ፈላጊ ነው ማለትን በጭራሽ አያስይዝም ለምሳሌ አየር ከምድር በላይ ነው ነገር ግን ከምድር ፈላጊ አይደለም፡፡ጠቅለል አድርገን ስናየው የነዚህ መፅሀፎች ትልቅ ችግር አላህ ስለአንድ ባህሪው በቁርኣን ውስጥ ሲናገር ይህንን ባህሪ ከፍጡራን ባህሪ ጋር ያመሳስሉታል ከዚያም ይህ ባህሪ ከፍጡራን ባህሪ ጋር ይመሳሰላልና ለአላህ አይገባውም በማለት የአላህን ስምና ባህሪያትን ውድቅ ያደርጋሉ፡፡ነገር ግን እንደ አህለሱናዎች አላህ የፍጡራንን የማይመስል ስምና ባህሪያቶች አሉት ብለው አፅድቀው ቢያልፉ ምንኛ በታደሉ ነበር ምክንያቱም አላህ እንዲህ ይላል፡-

١ ﴿لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ ١١﴾

((የሚመስለው ምንም ነገር የለም::እርሱም ሰሚ እንዲሁም ተመልካች ነው)) (አሸሹራ 11)

﴿ ءَأَمِنتُم مَّن فِي ٱلسَّمَآءِ أَن يَخۡسِفَ بِكُمُ ٱلۡأَرۡضَ فَإِذَا هِيَ

تَمُورُ ١٦ ﴾

((በሰማይ ውስጥ ያለው (አላህ) በናንተ ላይ ምድርን ቢደርብባችሁ እርሱን ትተማመናላችሁን?)) (አል ሙልክ 16)

በሌላም የቁርኣን አንቀጽ ላይ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلرَّحۡمَٰنُ عَلَى ٱلۡعَرۡشِ ٱسۡتَوَىٰ ٥ ﴾

((አረህማን በዐርሹ ላይ ከፍ አለ)) (ጣሀ 5)

15. አላህ ከኛ ጋር ነውን? ከተባልክ

አላህ ከሰማያቶች በላይ በዐርሹ ላይ ከፍ ከማለቱ ጋር በእውቀቱ፣ በማካበቡ በእርዳታውና በድጋፍ ከኛ ጋር ነው በል። ለዚህ ማስረጃ ይህ የአላህ ንግግር ነው፡-

﴿ وَهُوَ مَعَكُمۡ أَيۡنَ مَا كُنتُمۡۚ ﴾

((እርሱም የትም ብትሆኑ ከናንተ ጋር ነው [7])) (ሐዲድ -4)

በሌላም የቁርኣን አንቀጽ አላህ ለነብዩ ሙሳና ሀሩን እንዲህ ብሏቸዋል፡-

﴿ إِنَّنِي مَعَكُمَآ أَسۡمَعُ وَأَرَىٰ ٤٦ ﴾

((እኔ በእርግጥ ከናንተ ጋር ነኝና እሰማለው አያለውም))
(ጠሀ 46)

16. **የወሊይ ትርጉም ምንድነው?** ከተባልክ

አላህን የሚፈራና አማኝ የሆነ ሰው ሁሉ ወሊይ ነው በል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል:-

---

(7) ይህንን የቁርኣን አንቀጽ ማስረጃ በማድረግ አንዳንድ ሰዎች አላህ ሁሉም ቦታ አለ እያሉ ሙስሊሞችን ሲያወናብዱ ይስተወላሉ ነግር ግን አንቀጹ የሚያመለክተው የአላህ አብሮነት በእውቀቱ እንደሆነ ነው ምክንያቱም አንቀፁ እየተናገረ ያለው በእውቀት ዙሪያ ነውና፡፡

﴿أَلَآ إِنَّ أَوۡلِيَآءَ ٱللَّهِ لَا خَوۡفٌ عَلَيۡهِمۡ وَلَا هُمۡ

يَحۡزَنُونَ ٦٢ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَكَانُواْ يَتَّقُونَ ٦٣﴾

((ንቁ የአላህ ወዳጆች (ወሊዮች) በነርሱ ላይ ፍርሀት የለባቸውም እነርሱም አያዝኑም (እነርሱም) እነዚያ ያመኑትና ይፈሩት የነበሩ ናቸው::)) (ዩኑስ 62 --63)

17. **ከፍጥረታት ውስጥ መልካም ሰዎች እነማን ናቸው? መጥፎዎቹስ እነማን ናቸው?** ከተባልክ

መልካሞቹ አላህን በብቸኝነት የሚያመልኩ አማኞች ሲሆኑ መጥፎዎቹ አይሁዶችንና ነሳራዎችን የመሰሉ ካፊሮች እንዲሁም አጋሪዎች ለምሳሌ ጣዖትንና ቀብርን የሚያመልኩ (የሚገዙ)፣ ወደ ክህደት የተመለሱ (ሙርተዶች)፣እና መላሒዳዎች[8] ናቸው በል

---

(8) መላሒዳዎች ማለት ቁስ አምላኪዎች ሲሆኑ ስለነዚህ ሰዎች **ሼኽ ኢብኑ ባዝ (አላህ ይዘንላቸው) አል ዐቂደቱ አስሰሒሃ በተባለው ኪታባቸው ገፅ 24 ላይ** እንዲህ ይላሉ ፦ « መልእክተኞችን የመጡበትን መንገድንና ትክክለኛውን ዐቂዳ ከሚፃረሩት የኩፍር እምነቶች ውስጥ በአሁን ዘመን

ለዚህ ማስረጃ ይህ የአላህ ንግግር ነው፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ خَيۡرُ ٱلۡبَرِيَّةِ ٧ جَزَآؤُهُمۡ عِندَ رَبِّهِمۡ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۖ رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهُمۡ وَرَضُواْ عَنۡهُۚ ذَٰلِكَ لِمَنۡ خَشِيَ رَبَّهُۥ ٨ ﴾

((እነዚያ ከመፅሐፍ ሰዎች የካዱትና አጋሪዎቹ በጀሀነም እሳት ውስጥ ናቸው በውስጧ ዘውታሪዎች ሲሆኑ እነዚያ

የሌኒንና ማርክስ እንዲሁም የሌሎች መሪዎች ተከታይ የሆኑ ሰዎች መንገድ የሆነው የኢልሓድ መንገድ ነው።የነዚህ ሰዎች መሰረታዊ እምነታቸው ቁሳዊ ህይወት እንጂ አምላክ የሚባል ነገር የለም የሚል ሲሆን በሌላም በኩል ከሞት በኋላ መቀስቀስ የለም ፡ጀነት የለም ጀሀነም የለም ይላሉ የነርሱን መፅሐፍ ያነበበና እነርሱ ያሉበትን እምነት የተማረ ሰው ሐይማኖቶችን በአጠቃላይ እንደሚዳረሩና በዱንያም በአኼራም መጨረሻቸው የከፋ መሆኑን በእርግጠኝነት ያውቃል። ››

እነርሱ ከፍጥረት ሁሉ ክፉ ናቸው። እነዚያ ያመኑትና መልካሞችንም የሰሩት እነዚያ እነሱ ከፍጥረት ሁሉ በላጭ ናቸው።)) (አል በይነህ 6-7)

18. **ከወንጀሎች ሁሉ ከባድ ምንድነው?** ከተባልክ

ከወንጀሎች ሁሉ ከባድ በአላህ ላይ ማጋራት (ሽርክ) ነው በል፡

ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغۡفِرُ أَن يُشۡرَكَ بِهِۦ وَيَغۡفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ

لِمَن يَشَآءُ ﴾

((አላህ በርሱ ማጋራትን በፍፁም አይምርም ከዚህ ሌላ ያለውንም (ወንጀል) ለሚሻው ሰው ይምራል) [9] (አንኒሳ 48)

በሌላም የቁርኣን አንቀጽ አላህ እንዲህ ይላል፡-

---

(9) ይህ አንቀጽ ሽርክ ከወንጀሎች ሁሉ ከባድ እንደሆነ ያመላክታል ምክንያቱም አላህ ሽርክ የሚሰራን ሰው አልምረውም ዘላለም እሳት ውስጥ ይቃጠላል እያለ ነው ይህ ደግሞ ከባድነቱን ያመላክታል።

﴿ بَلَىٰ مَن كَسَبَ سَيِّئَةً وَأَحَٰطَتۡ بِهِۦ خَطِيٓـَٔتُهُۥ فَأُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴾

((... መጥፎን (ክህደትን) የሠራ በርሱም ሀጥያቱ የከበበችው ሰው እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው::)) (10) (አል በቀራ 81)

19. ወደ ምድር የተላከው የመጀመሪያው የአላህ መልክተኛ ማነው? ከተባልክ

ወደ ምድር የተላከው የመጀመሪያው መልክተኛ ነብዩላህ ኑህ ነው በል ለዚህም ማስረጃ የትንሳኤ እለት የሰው ልጆች ለኑህ እንዲህ ይሉታል፡-

يَا نُوحُ أَنْتَ أَوَّلُ الرُّسُلِ إِلَى الأَرْضِ وَسَمَّاكَ اللَّهُ عَبْدًا

(10) . ሰውን ልጅ ሸርክ እንጅ ሌላ ወንጀል በአጠቃላይ አያካብበውምና

شَكُورًا اشْفَعْ لَنَا إِلَى رَبِّكَ أَلاَ تَرَى مَا نَحْنُ فِيه أَلاَ تَرَى

مَا قَدْ بَلَغَنَا

((አንተ ኑህ ሆይ አላህ ወደ ምድር የላከክ የመጀመሪያ መልክተኛ አንተ ነህ አላህም አመስጋኝ ባሪያ ብሎ ጠርቶሀል ያለንበትንና የደረሰብንን ጭንቅ አትመለከትምን? ወደ ጌታህ አታማልደንምን?))

20. **የመጨረሻው መልክተኛ ማነው?** ከተባልክ

የመጨረሻው መልክተኛ ነብያችን መሐመድ(صلى الله عليه وسلم) ናቸው በል

ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن

رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ﴾

((መሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም ግን የአላህ መልክተኛና የነብያት ማሳረጊያ ነው)) (አል አህዛብ 40

ሁለተኛ ደረጃ

ጥ 1. የዲን (ሃይማኖት) ደረጃዎች ስንት ናቸው?

መ - የዲን ደረጃዎች ሦስት ናቸው እነሱም፡-

1. ኢስላም
2. ኢማን
3. ኢህሳን

ለዚህም ማስረጃ የጂብሪል ሐዲስ በመባል የሚታወቀው ረጅሙ ሐዲስ ነው (11)

---

(11) ይህ ረጅም ሐዲስ እንደሚከተለው ነው፡-

ዑመር ኢብኑ አልኸጣብ እንዳስተላለፉት ‹‹ከእለታት አንድ ቀን ከአላህ መልክተኛ (صلى الله عليه وسلم) ጋር ተቀምጠን ሳለ አንድ በጣም ነጭ የሆነ ልብስ የለበሰ ፀጉሩ በጣም የጠቆረ ምንም አይነት የመንገደኛ ምልክት የማይታይበትና ከኛም መካከል ማንም ሰው የማያውቀው የሆነ ሰው ብቅ አለ፡፡ ጉልበቱን ከነብዩ ጉልበት ጋር አስደግፎ ተቀመጠ መዳፎቹን ደግሞ ታፋዎቹ ላይ አደረገ፡፡ ‹‹መሐመድ ሆይ ስለ ኢስላም ንገረኝ›› አለ የአላህ መልክተኛም ***‹‹ኢስላም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለና መሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሰላትን መስገድ፣ ዘካ (ምፅዋት) መስጠት የረመዳንን ወር መፆም ለቻለ ሰው ሐጅ ማድረግ››***

ጥ2. ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው?

አሉት። ጠያቂውም ‹‹እውነት ብለሀል›› አለ። (ሰሀቦችም) ‹‹እሳቸውን እየጠየቀ እውነት መናገራቸውን በማረጋገጡ በዚህ ድርጊቱ በጣም ተገረምን›› አሉ። ጠያቂው ቀበል አድርጎ ‹‹ስለ ኢማን ንገረኝ›› አላቸው እሳቸውም ***‹‹ኢማን ማለት በአላህ በመላእክቶቹ በመፃሕፍቶቹ በመልክተኞቹ በመጨረሻ ቀንና ቀድሞውኑ በተወሰኑት የአላህ ውሳኔዎች (በቀደር) ማመን ነው››*** *አሉት እሱም ‹‹እውነት ብለሀል›› አለ ቀጥሎም ‹‹ስለ ኢህሳን (መልካም ምግባር) ንገረኝ›› አላቸው። እሳቸውም* ***‹‹ኢህሳን ማለት አላህን እንደምታየው ሆነህ ማምለክ አንተ ባትመለከተው እርሱ ይመለከትሀል››*** *አሉት ከዚያም ‹‹ስለ ሰዓቲቱ ንገረኝ›› አላቸው እሳቸውም* ***‹‹ተጠያቂው ከጠያቂው የበለጠ እውቀት የለውም››*** *አሉት ‹‹እሺ ስለ ምልክቶቹ ንገረኝ›› አላቸው። እሳቸውም* ***‹‹በባርነት ውስጥ ያለች ሴት አለቃዋን ትወልዳለች ጫማ የሌላቸው፣ የታረዙ፣ ድሆችና እረኞች የነበሩ ሰዎች ታላላቅ ህንፃዎችን ለመገንባት ሲፎካከሩ ታያለህ››*** *አሉት ከዚያም (ጠያቂው) ሄደ። እኔ ጥቂት ከቆየሁ በኋላ የአላህ መልክተኛ ‹‹ጠያቂው ማን እንደሆነ ታውቃለህን›› ሲሉ ጠየቁኝ እኔም ‹‹አላህና መልክተኛው ያውቃሉ›› አልኳቸው እሳቸውም* ***‹‹እሱ በእርግጥ ጂብሪል ነው ሃይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ነው የመጣው።›› አሉኝ (ቡኻሪ ዘግበውታል)***

መ. ኢስላም ማለት አላህን ብቸኛ በማድረግ ለርሱ ታዛዥ መሆን በታዛዥነትም ለርሱ መጎተት ከሽርክና ከአራማጆቹም ራስን ማራቅና ማጥራት ነው። ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَإِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ فَلَهُۥٓ أَسْلِمُواْ ۗ وَبَشِّرِ ٱلْمُخْبِتِينَ

((አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው ለርሱም ብቻ ታዘዙ (ለአላህ)ተዋራጆችንም አብስራቸው))(አል-ሀጅ 34)

ጥ 3. ኢማን ማለት ምን ማለት ነው

መ. ኢማን ማለት በምላስ መናገርን በልቦና ማረጋገጥንና በአካል መተግበርን የሚያካትት ሲሆን መልካምን በመስራት ሲጨምር ወንጀልን በመስራት ደግሞ ይቀንሳል።[12]

(12) ኢማን መልካም ሥራን በመስራት እንደሚጨምር ማስረጃው አላህ እንዲህ ይላል፡-

ኢማን ብዙ ቅርንጫፎች እንዲሁም ስድስት መሰረቶች (አርካኖች) አሉት ለዚህ ማስረጃ ይህ የአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) ንግግር ነው::

« الإِيمَانُ بِضْعٌ وَسَبْعُونَ أَوْ بِضْعٌ وَسِتُّونَ شُعْبَةً فَأَفْضَلُهَا قَوْلُ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَأَدْنَاهَا إِمَاطَةُ الأَذَى عَنِ الطَّرِيقِ وَالْحَيَاءُ شُعْبَةٌ مِنَ الإِيمَانِ ».

((ኢማን ሰባ ምናምን ወይም ስልሳ ምናምን ቅርንጫፎች አሉት ትልቁ ለኢላሃኢላላህ የሚለው ንግግር ሲሆን ትንሹ ደግሞ አስቸጋሪ ነገርን ከመንገድ ማስወገድ ነው:: ሀፍረት እራሱ ከኢማን ቅርንጫፎች ውስጥ ነው::)) ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል

﴿ إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتْهُمْ إِيمَٰنًا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ ٢ ﴾

((ፍፁም አማኞች ማለት እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ ኢማንን የሚጨምሩላቸውና በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው::)) (አል አንፋል 2)
ለመቀነሱ ደግሞ የመጨመሩ ማስረጃ እራሱ ማስረጃ ይሆነዋል ምክንያቱም ከመጨመሩ በፊት ቀንሶ ነበርና

ጥ4. ኢህሳን (መልካም ምግባር) ማለት ምን ማለት ነው?

መ. ኢህሳን ማለት አላህን እንደምትመለከተው ሆነህ እርሱን መገዛት (ማምለክ) ነው። አንተ እንደምትመለከተው ካልሆንክ እርሱ ይመለከትሀል።

ስለ ኢህሳን በጠየቃቸው ጊዜ እንዲህ ብለውታል፦

« أَنْ تَعْبُدَ اللَّهَ كَأَنَّكَ تَرَاهُ فَإِنْ لَمْ تَكُنْ تَرَاهُ فَإِنَّهُ يَرَاكَ ».

((ኢህሳን አላህን እንደምትመለከተው ሆነህ እርሱን መገዛት ነው አንተ እንደምትመለከተው ካልሆንክ እርሱ ይመለከትሀል።

ጥ 5. ስራ (ዒባዳ) አላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው መስፈርቱ ምንድነው?

መ. ማንኛውም ስራ (ዒባዳ) አላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ***ሦስት*** መስፈርቶች (ቅድመ ሁኔታዎች) ያስፈልጉታል እነርሱም፦

1. **ኢስላም መሆን** ምክንያቱም ከሀዲ (ካፊር) የሆነ ሰው አላህ ስራውን አይቀበለውም (ምንዳ አያገኝበትም)። ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ وَقَدِمْنَآ إِلَىٰ مَا عَمِلُوا۟ مِنْ عَمَلٍ فَجَعَلْنَٰهُ هَبَآءً مَّنثُورًا ﴾

((ከስራም ወደ ሰሩት እናስባለን የተበተነ ትብያም እናደርገዋለን)) (አል ፉርቃን 23)

2. **ኢኽላስ (ስራን ለአላህ ብቻ ማድረግ)**[13] ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

(13) ኢኽላስ ማለት የምንሰራውን ማንኛውም ዒባዳ ለአላህ ብቻ ማጥራት ይዩልኝና ይስሙልኝን በመተው ከአላህ የሚገኘውን አጅር (ምንዳ) ብቻ መከጀል ሲሆን ኒያችን ከዚህ ውጭ ከሆነና የሰዎችን ሙገሳ እንዲሁም የዱንያን ጥቅም የምናስቀድም ከሆነ አላህ እንዲህ ይላል ፡-

﴿ مَن كَانَ يُرِيدُ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا وَزِينَتَهَا نُوَفِّ إِلَيۡهِمۡ أَعۡمَٰلَهُمۡ فِيهَا وَهُمۡ فِيهَا

لَا يُبۡخَسُونَ ١٥ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَيۡسَ لَهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ إِلَّا ٱلنَّارُ ۖ وَحَبِطَ مَا

صَنَعُواْ فِيهَا وَبَٰطِلٞ مَّا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴾

((የዱንያን ህይወትና ጌጧን የሚፈልጉ የሆኑ ሰዎች ሥራዎቻቸውን(ምንዳዋን) በእርሷ ውስጥ ይሠጣቸዋል እነርሱም በእርሷ ውስጥ ምንም አይጎድልባቸውም እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ከእሳት በስተቀር የሌላቸው ናቸው የሰሩትም ሥራ በእርሷ ውስጥ ተበላሸ። (በዱንያ እያሉ) ሲሰሩት ነበረው በጎ ሰራ ብልሹ ነው።)) (ሁድ 15-16)

﴿ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ ﴾

((ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ አጥሪዎች ሆነው እንዲገዙት እንጂ አልታዘዙም)) (አል በይነህ 5)

3. **የአላህን መልክተኛ መከተል፡- ለዚህም ማስረጃ የአላህ መልክተኛ እንዲህ ብለዋል**

(من عمل عملاً ليس عليه أمرنا فهو رد

((የኛ ትዕዛዝ የሌለበትን ስራ የሰራ ሰው (ስራው) ተመላሽ ነው))

ጥ6. የአላህ መልክተኞች በአጠቃላይ የተጣሩት (ዳዕዋ ያደረጉት) ወደ ምንድነው?

መ. መልክተኞች የተጣሩት አላህን በብቸኝነት ወደመገዛትና በርሱም ላይ ምንንም ወደ አለማጋራት (አለማሻረክ) ነው።።

ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِي كُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَ ﴾

((በየህዝቡም ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ ጣኦትንም ራቁ›› በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል)) (አል ነህል 36)

ጥ7. ዒባዳ ማለት ምን ማለት ነው?

መ. ዒባዳ ማለት ከንግግርም ይሁን ከተግባር ድብቅም ይሁን ግልፅ ለማንኛውም አላህ ለሚወደው ነገር የተሠ ስም ነው፡ ማስረጃውም አላህ በተከበረው ቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِن تَكۡفُرُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِيٌّ عَنكُمۡۖ وَلَا يَرۡضَىٰ لِعِبَادِهِ ٱلۡكُفۡرَۖ وَإِن تَشۡكُرُواْ يَرۡضَهُ لَكُمۡۗ ﴾

((ብትክዱ አላህ ከናንተ የተብቃቃ ነው ለባሪያዎቹም ክህደትን አይወድም ብታመሰግኑም እርሱን ይወድላችኋል)) [14] (አዝ ዙመር 7)

---

(14) ይህ የቁርኣን አንቀፅ አንደሚያመለክተን አላህ በራሱ የተብቃቃ ጌታ ነው የሰው ልጆች ሁሉ ለአላህ ቢያምኑ ከአላህ ንግስና ላይ የሚጨምሩት

- ምስጋና (ሹክር) የልብንም የምላስንም የአካልንም ስራ ያጠቃልላል[15]

ጥ8. ዒባዳ (አምልኮት) ለስንት ይከፈላል

መ. ዒባዳ ለአምስት ይከፈላል እነሱም፡

1. የንግግር ዒባዳ :- ለምሳሌ ሸሀደተይንን መናገር[16]፣ ቁርአንን መቅራት፣ ዱዐ ማድረግ ከትክክለኛ ሐዲሶች የተገኙ አዝካሮችን መዘከር

ነገር የለም ሁሉም ቢክዱም ከርሱ ንግስና የሚቀንሱት ነገር የለም መልካም ቢሰሩ ለራሳቸው ነው ባይሰሩም ችግሩ በራሳቸው ላይ ነው አላህ ማንንም የሚበድል ጌታ አይደለም።

(15) ለዚህ አባባል ምሳሌ ለመስጠት ያህል አንድ ሰው በሀላል መንገድ ገንዘብን ቢያገኝ **በልቡ** ይህንን ገንዘብ አላህ እንደሰጠው ያምናል **በምላሱ** አልሀምዱሊላሂ ይላል **በአካሉ** ደግሞ የምስጋና ሱጁድ ያደርጋል በተጨማሪም ይህንን ገንዘብ አላህ በሚፈልገው ቦታ ያውለዋል።

(16) ሸሀደተይን ማለት አሽሀዱአላአላሀኢለላህ ወአነሙሐመደረሱሉላህ የሚለው ንግግር ነው።ትርጉሙም **‹‹ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ››** ማለት ነው።

2. እምነታዊ ዒባዳ ፡- ለምሳሌ አላህ የፈጠረ ሲሳይን (ሪዝቅን) የሚሰጥ ህያው የሚያደርግና የሚገድል እንዲሁም የባሮችን ጉዳይ በአጠቃላይ የሚያከናውን መሆኑን አንድ ሙስሊም ማመኑ ከዚህ ውስጥ ይካተታል

3. አካላዊ ዒባዳ፡- ለምሳሌ ለሰላት መቆም፣ሩኩዕ ማድረግ፣ ሱጁድ ማድረግ፣ ፆም መፆም፣ የሀጅ ስራዎችን መስራት፣ ለአላህ ብሎ መሰደድ (ሂጅራ)፣ በአላህ መንገድ ላይ መታገል

4.የገንዘብ ዒባዳ ፡- ለምሳሌ ዘካን ሰደቃ መስጠት

5. የመተው ዒባዳ፡- ለምሳሌ አንድ ሙስሊም አላህን በመታዘዝና የእርሱን ፊት በመፈለግ እርሱ የከለከላቸውን እንደ ሽርክ፣ ቢድዓ እና ሌሎችንም እኩይ ተግባራት መራቅ

ጥ9. ቢድዓ ምንድነው?

መ. ከቁርኣንና ከሐዲስ መረጃ ሳይኖረው ከሰለፎችም ፋና ሳይገኝ አላህን ለመገዛትና ወደርሱ ለመቃረብ ተብሎ የአላህ መልክተኛ ከሞቱ በኋላ የተፈጠረ ማንኛውም እምነት ወይም ተግባር ወይንም ንግግር ቢድዓ (መጤ) ይባላል።

ጥ10. የቢድዓ ሁክም (ፍርድ) ምንድነው?

መ. ሁሉም ቢድዓ ጥመት ነው ሁሉም ጥመት የእሳት ነው[17] ሁሉም ቢድዓ ሀራም (ክልክል) ነው። ነገር ግን ይህ ክልከላ (ሀራምነት) እንደቢድዓ ዓይነቱ ይበላለጣል። ከነርሱ ውስጥ ለምሳሌ ፦

1. **ትልቁ ቢድዓ-** ይህ የቢድዓ ዓይት ክህደት ውስጥ የሚከት (የሚያከፍር) ሲሆን ሰውዬውን ከእስምልና ውጭ ያደርገዋል ለምሳሌ ፈጣሪና ፍጡር እኩል ናቸው የሚለው እምነት እንዲሁም ወሰን የተላለፉ የጀህምያዎችና የሙዕተዚላዎች[18] ንግግሮች እዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

---

(17) .ይህ ንግግር ኢርባድ ኢብኑ ሳሪያ ያስተላለፈውና ቲርሚዚ የዘገበው የአላህ መልክተኛ ንግግር ነው።

(18) **ጀህምያዎች፦** መስራቻቻው **ጀህም ኢብኑ ሰፍዋን አስሰመርቀንዲ** ሲሆን እርሱ ይህንን መንገድ የተማረው **ጀዕድ ኢብኑ ዲርሀም** ከሚባል ሰው ነው። ቢድዓ ከሆነው ንግግሮቻቸው ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፦

1. አላህና መልክተኛው(صلى الله عليه وسلم) ያፀደቁትን የአላህን ስሞችና ባህሪያት ውድቅ ያደርጋሉ።

2. እነርሱ ዘንድ ኢማን ማለት ማወቅ ማለት ነው ስለዚህ በነርሱ አባባል አንድ ሰው አላህን ካወቀው ኢማን አለው ይሉታል ትክክለኛው የኢማን ትርጉም ግን በገፅ 36 ላይ የተቀመጠው የአህለ ሱና ትርጉም ነው።

3 .ቁርኣን ፍጡር ነው ይላሉ።

2 .ትንሹ ቢድዓ፡- ይህም የቢድዓ ዓይነት ጥመት ነው ነገርግን ሰውዬውን ከእስልምና ውጪ አያደርገውምን(አያከፍረውም)፡፡ ለምሳሌ ፡- በጀናዛ (አስክሬን) ላይ ድምፅን ከፍ አድርጎ ቁርኣንን መቅራት [19]

ሙዕተዚላዎች፡- የነዚህ መስራችና መሪ ደግሞ **ዋሲል ኢብኑል ዓጣ አል ገዛል** ሲሆን ይህ ሰው የአህለሱና መንገድ የሆነውን የሐሰነልበስሪ መንገድ በመተው የራሱን ቢድዓ የሆነ አመለካከት በመያዝ ተገንጥሎ የራሱን ቡድን መስርቷል፡፡ ከንግግሮቻቸው ውስጥ፡-

1. የአላህን ባህሪያት ውድቅ በማድረግ ስሞቹን ግን ያፀድቃሉ፡፡
2. እንደ ጀህምያዎች ቁርኣን ፍጡር ነው ይላሉ፡፡
3. ከትላልቅ ወንጀሎች ውስጥ አንዱን የሰራ ሙስሊም ካፊር ሙእሚንም አይደለም ይላሉ፡፡

(19) ኢማሙ አንነወዊይ ሪያዱ ሳሊሒን በሚባለው ኪታባቸው ውስጥ ኢማሙ ሻፊዒይ ቀብር ላይ ቁርኣንን መቅራት ይወደዳል ብለዋል በማለት አስቀምጠዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ንግግር ትክክል እንዳልሆነና ኢማሙ ሻፊዒይም ይህንን እንደማይደግፍ ብዙ ዑለማዎች ተናግረዋል፡፡ ከነዚህ ዑለማዎች ውስጥ ኢብኑ ተይሚያ እንዲህ ይላል፡-((**በዚህ ጉዳይ ላይ ከኢማሙ ሻፊዒይ ምንም ዓይነት ንግግር አልተገኘም ምክንያቱም ይህ ተግባር እርሳቸውም ዘንድ ቢድዓ ነውና...**)) (አህካሙል ጀናኢዝ ከሚባለው የሼኽ አልባኒይ ኪታብ የተወሰደ)

ይህ ተግባር ከሰሀቦችም ሆነ ከታቢዒዮች አልተገኘም ስለዚህ በነርሱ ጊዜ ዲን ያልነበረ ነገር ዛሬም ዲን ሊሆን አይችልም፡፡

ጥ 11. ከባዱ በደል ምንድነው?

መ. ከባዱ በደል ሽርክ (በአላህ ላይ ማጋራት) ነው።።

ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّ ٱلشِّرۡكَ لَظُلۡمٌ عَظِيمٞ ١٣﴾

((ማጋራት ትልቅ በደል ነው)) (ሉቅማን 13)

ጥ 12. ተውሒድ ማለት ምን ማለት ነው?

መ. ተውሒድ ማለት አላህን እርሱ በተለየበት ማለትም በጌትነቱ በአምላክነቱ እንዲሁም በስሞቹና በባህሪያቶቹ መነጠል (ብቸኛ ማድረግ) ነው

ጥ 13. ተውሒድ በስንት ይከፈላል

መ. ተውሒድ በሦስት ይከፈላል እነሱም

1. **ተውሒድ አሩቡቡያ (በጌትነቱ ብቸኛ ማድረግ)**[20]

---

(20) ይህ ማለት የሚፈጥር፣ የሚገድል፣ የሚያበላ፣ የሚያጠጣ፣ የሚያስተናብር እርሱ ብቻ ነው ብሎ ማመን ሲሆን ነገር ግን በነዚህ

2. ተውሒድ አልኡሉሁያ (በአምልኮ ብቸኛ ማድረግ)

ነገራቶች ብቻ ማመኑ አንድን ሰው እስልምና ውስጥ አያስገባውም ምክንያቱም አላህ የመካ ሙሽሪኮች በነዚህ ነገሮች እንደሚያምኑ እንዲህ ሲል ነግሮናል

﴿ وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ لَيَقُولُنَّ ﴾

((ሰማይና ምድርን የፈጠረ ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው‹‹አላህ ነው›› ይሉሀል)) (አዝዙመር 34)

ነገር ግን የአላህ መልክተኛ አምልኮትን ለአላህ ብቻ አድርጉ ሲሏቸው ከመቀበል ይልቅ መገረማቸውን አላህ በቁርኣኑ ነግሮናል እንዲህ አሉ፡-

﴿ أَجَعَلَ ٱلْآلِهَةَ إِلَٰهًا وَٰحِدًا ۖ إِنَّ هَٰذَا لَشَىْءٌ عُجَابٌ ٥ ﴾

((‹‹አማልክቶቹን አንድ አምላክ አደረጋቸውን? ይህ አስገራሚ ነገር ነው›› አሉ)) (ሳድ 5)

ስለዚህ የላኢላሃኢለላህ ዋና ዕንሰ ሐሳብ አላህ ያበላል ያጠጣል ሳይሆን አላህን በብቸኝነት መገዛትና ከሽርክ መራቅ መሆኑን ሁሉም ሙስሊም ጠንቅቆ ሊረዳ ይገባል፡፡

3. ተውሒድ አልአስማኢ ወሲፋት (በስምና በባሪያቶቹ ብቸኛ ማድረግ)

ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ١ ﴾

((በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው))

(አል ፋቲሀ 1)

﴿ رَّبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَا فَٱعۡبُدۡهُ وَٱصۡطَبِرۡ لِعِبَٰدَتِهِۦۚ

هَلۡ تَعۡلَمُ لَهُۥ سَمِيّٗا ٦٥ ﴾

((እርሱ) የሰማያትና የምድር በሁለቱም መካከል ላለው ሁሉ ጌታ ነውና ተገዛው (እርሱን) በመገዛት ላይም ታገስ ለርሱ ሞክሼን ታውቃለህን?)) (መርየም 65)

እነዚህ ሁለት የቁርኣን አንቀፆች ሦስቱን የተውሒድ ዓይነቶች በውስጣቸው አቅፈዋል።

ጥ 14. ተውሒድ አሩቡቡያ ትርጉሙ ምንድን ነው?

መ. ትርጉሙ አላህን በስራዎቹ ብቸኛ ማድረግ። ለምሳሌ ያህል በመፍጠሩ፣ በመቆጣጠሩ፣ በማስተናበሩ

ጥ 15. ተውሒድ አልኡሉሂያ ትርጉሙ ምንድነው?

መ. ትርጉሙ አላህን በባሮች ስራ ብቸኛ ማድረግ ሲሆን ይህ ማለት በአምልኮታቸው አላህን መነጠል (ብቸኛ ማድረግ) ማለት ነው።

ጥ 16. ተውሒድ አልአስማኢ ወሲፋት ትርጉሙ ምንድነው?

መ. አላህን እርሱ ባልነገረንና መልክተኛውም ባላስተማሩን ስሞች አለመጥራት እንዲሁም እርሱ እራሱን ባልገለፀበትና መልክተኛውም እርሱን ባልገለፁበት ባህሪ እርሱን አለመግለፅ[21]

---

(21) ይህ ማለት በተቃራኒው አላህን እራሱን በገለፀበትና መልክተኛው እርሱን በገለፁበት ባህሪያትና ስሞች ሳናመሳስል ሁኔታውን ሳንጠይቅና ሳናራቁት(ውድቅ ሳናደርግ) አላህ በሚገባው መልኩ ማፅደቅ ማለት ነው።

ሦስተኛ ደረጃ

1. በአላህ ማመን

በአላህ ማመን ሲባል አላህ በመኖሩ ማረጋገጥንና በጌትነቱ በአምላክነቱና በስምና ባህሪያቶቹ ማመንን ያጠቃልላል፡፡

❖ ***በአላህ ማመን አራት ነገሮችን ያካትታል***

1. አላህ በመኖሩ ማመን
2. በአላህ ጌትነት ማመን
3. በአላህ አምላክነት ማመን
4. በአላህ ስምና ባህሪያት ማመን

2. በመላእክት ማመን

በመላእክት ማመን ማለት በመኖራቸው እርግጠኛ መሆን ሲሆን እነርሱ የተከበሩ የአላህ ባሮች ናቸው አላህ ያዘዛቸውን አያምፁትም የታዘዙትንም ይተገብራሉ፡፡

❖ ***በመላእክት ማመን አራት ነገሮችን ያካትታል***

1. በመኖራቸው ማመን እነርሱ የተከበሩ የአላህ ባሮች ናቸው፡
2. ከነርሱ ውስጥ እንደ ጂብሪል ስሙን ያወቅነውን በስሙ እናምለናን በማናውቀው ደግሞ በጥቅሉ በሁሉም እናምናለን፡፡

3. ከባህሪያታቸው ውስጥ ባወቅነው ማመን ለምሳሌ ጅብሪል አድማስን የሚሸፍን ስድስት መቶ ክንፍ አለው።[22]

4. በአላህ ትዕዛዝ ከሚሰሩት ስራዎች ውስጥ ባወቅነው ማመን ለምሳሌ አላህን ማወደስ ያለ ምንም እረፍትና መሰልቸት ቀን ከለሊት እርሱን መገዛት ከስራዎቻቸው ውስጥ ይገባሉ።

---

(22) አንዳንድ ከትክክለኛው መንገድ የጠመሙ ሰዎች መላእክቶች ማለት በፍጡራን ውስጥ ያሉ ድብቅ የሆኑ ጥሩ መንፈሶች እንጂ አካል ያላቸው ፍጥረቶች አይደሉም በማለት ይቀጣጥፋሉ። ይህ እምነታቸው ቁርኣንና ሀዲስን ማስተባበል ነው ምክንያቱም አላህ እንዲህ ይላል፡

﴿ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ جَاعِلِ ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ رُسُلًا أُو۟لِىٓ أَجْنِحَةٍ مَّثْنَىٰ

وَثُلَٰثَ وَرُبَٰعَ ۚ يَزِيدُ فِى ٱلْخَلْقِ مَا يَشَآءُ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿١﴾ ﴾

((ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ለሆነው እንዲሁም መላእክትን ባለሁለት ሁለት ባለ ሦስት ሦስትም ባለ አራት አራትም ክንፎች የሆኑ መልክተኞች አድራጊ ለሾነው አላህ ምስጋና ይገባው በፍጥረቱ ውስጥ የፈለገውን ይጨምራል አላህ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው)) (ፋጢር 1)

እነዚህና እነዚህን የመሰሉ ሌሎች የቁርኣንና የሐዲስ ማስረጃዎች መላእክቶች አካል እንዳላቸው በግልፅ ያስረዳሉ

ለከፊል መላእክቶች ደግሞ ለየት ያለ ስራ አላቸው ለምሳሌ

ጅብሪል - ለነብያትና ለመልክተኞች ከአላህ ወህይ ተቀብሎ ያመጣል

ሚካኢል - በዝናብና በማብቀል ላይ ተመድቧል

ኢስራፊል - በእለተ ትንሳኤ ቀንድ በመንፋት ተመድቧል

መለከል መውት (የሞት መልአክ) የሰውን ልጆች ነፍስ በመውሰድ ተመድቧል

ማሊክ - በእሳት ላይ ተመድቧል

3. በመፃህፍት ማመን

በመፃህፍት ማመን ማለት እነዚህ መፃህፍት እውነት መሆናቸውንና የአላህ ንግግር መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲሆን በውስጣቸው ብርሀንና ቀና መንገድን ይዘዋል ለተወረደላቸው ህዝቦችም ያብቃቃቸዋል።

በመፃህፍት ማመን አራት ነገሮች ያካትታል

1. ሁሉም መፃህፍት የወረዱት በእውነት ከአላህ ዘንድ መሆኑን ማመን የሚገባ ሲሆን ከነርሱ ውስጥ በአንዳች ነገር የካደ ሰው በሁሉም እንደካደ ይቆጠራል።
2. ከነዚህ መፃህፍት ውስጥ ስሙን ባወቅነው ማመን

ለምሳሌ፡-

- **ቁርኣን** - በነብያችን (صلى الله عليه وسلم) ላይ ተወርዷል
- የነብዩ **ኢብራሒም ሱሁፍ**
- በነብዩ ሙሳ ላይ የተወረደው **ተውራት**
- በነብዩ ዒሳ ላይ የተወረደው **ኢንጂል**
- **ዘቡር** ለነብዩ ዳውድ ተሰጥቷቸዋል

ስማቸውን ባላወቅነው መፃህፍት ደግሞ በጥቅሉ ማመን

3. በነዚህ መፃህፍት ውስጥ የተነገሩት ትክክለኛ ወሬዎችን እውነት ብሎ መቀበል ለምሳሌ ያህል

- ቁርኣን ውስጥ ያሉት የተለያዩ ነብያት ታሪኮች ከቁርኣን በፊት ካሉት መፅሐፍት ደግሞ ያልተበረዘና ያልተቀየረ ከሆነ እናምንበታለን ለዚህ ደግሞ ምሳሌ የሚሆነን የነብዩ መሐመድ (صلى الله عليه وسلم) ባህሪ በነዚህ ቀደምት መፅሐፍት ውስጥ መጠቀሱ ነው።

4. አጠቃላይ ቀደምት መፅሐፍት በታላቁ ቁርኣን ተሽረዋል

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّ مُصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيۡهِ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَمُهَيۡمِنًا عَلَيۡهِ ﴾

((ወደ አንተም መፅሐፍን ከበፊቱ ያለውን መፅሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በእውነት አወረድን))

(አልማኢዳ 48)

በቀደሙት መፅሐፍት ማመን በጥቅሉ ሲሆን ይህም በልብና በምላስ በማረጋገጥ ይሆናል። በቁርኣን ማመን ግን ዘርዘር ያለ ነው፤ ይህም ማለት በልብና በምላሳችን ከማረጋገጣችን በተጨማሪ ይዞት የመጣውን መከተል አለብን።

በትንሹም በትልቁም ጉዳይ በርሱ መፋረድ አለብን[23]

እንዲሁም ፍጡር ያልሆነ የተወረደ የአላህ ንግግር ነው

ጅምሩም ከርሱ ነው ወደርሱም ይመለሳል።

---

(23) ለሚገጥመን ማንኛውም ዲናዊም ይሁን ዱንያዊ አለመግባባቶች መፍትሔ ያለው በቁርአን ውስጥ ነው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَا ٱخۡتَلَفۡتُمۡ فِيهِ مِن شَيۡءٖ فَحُكۡمُهُۥٓ إِلَى ٱللَّهِ ﴾

((ከምንም ነገር ያ በርሱ የተለያያቹበት ነገር ፍርዱ ወደ አላህ ነው)) (አሸ ሹራ 10)

4. በመልእክተኞች ማመን

በመልክተኞች ማመን ማለት በመልክተኛነታቸውና በነብይነታቸው እርግጠኛ መሆን እነርሱ ከአላህ ተቀብለው በተናገሩት መልእክት እውነተኞች መሆናቸውን መቀበልና መልእክታቸውንም አላህ ባዘዛቸው መልኩ ግልፅ አድርገው ማድረሳቸውን ማመንን ያጠቃልላል።

በመልእክተኞች ማመን ሲባል አራት ጉዳዮን ያካትታል

1. መልእክተኝነታቸው ከአላህ የሆነ እውነት መሆኑን ማመን ከነርሱ ውስጥ በአንድ መልእክተኛ የካደ በሁሉም እንደካደ ይቆጠራል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

---

ይህ ማለት ወደ ቁርኣን ማለት ነው።

ነገር ግን ሙስሊሞች ዛሬ ለምናየው መለያየታቸው ትልቁ ምክንያት ይህን በመተዋቸውና ስሜታቸውንና የራሳቸውን ራዕይ ከቁርኣን በማስቀደማቸው ነው አልያማ ቁርአንና ሐዲስን ነክሶ የያዘና የተገበረማ በጭራሽ ሊለያይና ሊበታተን አይችልም። ለዚህ ነው የአላህ መልክተኛ ከናንተ ትንሽ የሚቆይ በሙስሊሞች መካከል ብዙ ልዩነቶችን ይመለከታልና በቁርአንና ሐዲስ ላይ አደራችሁን ያሉት።

﴿ كَذَّبَتۡ قَوۡمُ نُوحٍ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ١٠٥ ﴾

((የኑህ ህዝቦች መልእክተኞችን አስተባበሉ)) *(አሽ ሹዐራ 105)*

የኑህ ህዝቦች ኑህን ባስተባበሉ ወቅት ከርሱ ሌላ መልእክተኛ ካለመኖሩ ጋር አላህ ሁሉንም መልእክተኞች ያስተባበሉ ሰዎች አደረጋቸው።

ከዚህም በመነሳት ነብያችን መሐመድን ያስተባበሉትና ያልተከተሉት ክርስትያኖች ነብዩላህ ዒሳንም እንዳስተባበሉና እንደማይከተሉ ግልፅ ይሆናል በተለይም ነብዩላህ ዒሳ በመሐመድ መምጣት ከማበሰሩ ጋር

2. ከነርሱ ውስጥ ስሙን ባወቅነው መልእክተኛ እናምናለን ለምሳሌ መሐመድ፣ ኢብራሒም፣ ሙሳ፣ ዒሳ፣ ኑህ እነዚህ አምስቱ ኡሉል ዐዝም በመባል ይታወቃሉ። በሁሉም ላይ የአላህ ሰላትና ሰላም ይውረድ ስማቸውን ባላወቅነው ደግሞ በጥቅል ሁኔታ በሁሉም እናምናለን። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا رُسُلٗا مِّن قَبۡلِكَ مِنۡهُم مَّن قَصَصۡنَا عَلَيۡكَ

وَمِنۡهُم مَّن لَّمۡ نَقۡصُصۡ عَلَيۡكَ

((ካንተ በፊትም መልእክተኞችን በእርግጥ ልከናል ከነርሱ ባንተ ላይ የተረክንልህ አለ ከነርሱም ባንተ ላይ ያልተረክነው አለ)) (ጋፊር 78)

አላህ በቁርኣን ውስጥ የጠቀሳቸው ነብያቶችና መልእክተኞች ሀያ አምስት ሲሆኑ አስራ ስምንቱ በሱረቱ አልአንዐም ቁጥር 83 እስከ 86 የተጠቀሱ ሲሆኑ የቀሩት ሰባቱ ደግሞ በተለያዩ አንቀፆች ላይ ይገኛሉ።።

3. ከነርሱ ታሪክ ትክክል የሆነውን እውነት ነው ብሎ ማረጋገጥ

4. ከነርሱ ውስጥ ወደኛ በተላከው መልክተኛ ህግ መስራት እሳቸውም የሁሉም ነብያት መደምደሚያ (ማሳረጊያ) የሆኑትና ለሰው ልጆች በአጠቃላይ የተላኩት መሐመድ ኢብኑ አብደላ(صلى الله عليه وسلم) ናቸው።።

5. በመጨረሻው ቀን ማመን

በመጨረሻው ቀን ማመን ሲባል ይህ ቀን እንደሚከሰትና መምጣቱ አይቀሬ መሆኑን ማረጋገጥ እንዲሁም ለዚህ ቀን የሚያስፈልገውን ስንቅ መሰነቅ

በመጨረሻው ቀን ማመን አራት ጉዳዮችን ያካትታል

1. በማይቀሩትና ከርሷ በፊት በሚከሰቱት የቂያማ ምልክቶች ማመን እንዲሁም በሞትና ከርሱ በኋላ በሚመጡት በቀብር ፈተና፣ ፀጋና ቅጣት ማመን
2. በቀንድ እንደሚነፋ ከዚያም ፍጡራን በአጠቃላይ ከቀብራቸው እንደሚወጡና እንደሚሰበሰቡ ማመን
3. የሰው ልጆች መልካምና መጥፎ ስራ የተፃፈበት መዝገብ እንደሚበተን መልምና መጥፎ ስራቸው የሚመዘንበት ሚዛን እንደሚዘጋጅ እንዲሁም ምርመራ፣ ምንዳ፣ ሲራጥ፣ ሀውድና ሸፈዓ(ምልጃ) ... በመኖራቸው ማመን
4. በጀነትና በያዘችው ታላቅ ፀጋ በእሳትና ውስጧ ባለው ብርቱ ቅጣት ማመን

6. በቀደር ማመን

በቀደር ማመን ሲባል ማንኛውም መልካምም ይሁን መጥፎ ክስተቶች በአላህ ውሳኔ እንደሚከሰቱ ማረጋገጥ ነው። አላህ የፈለገውን አድራጊ ነው በርሱ ፍላጎት እንጂ ምንም ነገር ሊከሰት አይችልም። ከርሱ ፍላጎት የሚወጣ አንዳችም ነገር የለም በዓለም ውስጥ ከአላህ ውሳኔ የሚወጣ የለም። ለአንድም ሰው ከተወሰነው ውሳኔ መሸሻ የለውም በመፃፊያ ሰሌዳ ላይ

ከተፃፈውም የሚተላለፍ የለም ከፍ ያለው አላህ የባሪያዎቹን ተግባር ታዛዥነትንና አመፀኝነትን ፈጥሯል ከዚህም ጋር ግን ባሪያዎቹን በመልካም በማዘዝ ከመጥፎ ከልክሏቸዋል። በርሱ ላይ የሚገደዱ ሳይሆኑም ስራቸውን እንዲመርጡ አድርጓቸዋል ይልቁንስ ስራቸው የሚከሰተው ባላቸው ችሎታና ፍላጎት ልክ ነው። እነርሱንም ይሁን ችሎታቸውን ደግሞ አላህ ነው የፈጠረው በእዝነቱ የፈለገውን ሲያቀና በጥበቡ ደግሞ የፈለገውን ያጠማል እርሱ በሚሰራው አይጠየቅም እነርሱ ግን ይጠየቃሉ።

በቀደር ማመን አራት ጉዳዮችን ያካትታል

1. አላህ ከርሱ ስራ ጋር የተያያዘም ይሁን ከባሮች ስራ በጥቅልም ይሁን በዝርዝር መጀመሪያውንም ይሁን መጨረሻውን ሁሉንም ነገራቶች **<u>እንደሚያውቅ</u>** ማመን
2. አላህ ይህንን እውቀት የተጠበቀ በሆነው ሰሌዳ ውስጥ **<u>እንደፃፈው</u>** ማመን

የአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) እንዲህ ብለዋል፡-

((كتب الله مقادير الخلائق قبل أن يخلق السماوات والأرض بخمسين ألف سنة))

3. በአጠቃላይ በዓለም ላይ የሚከሰቱ ክስተቶች በአላህ **ፍላጎት** እንጂ እንደማይከሰቱ ማመን

4. በአጠቃላይ በዓለም ላይ ያለው ነገር በአካሉም በባህሪውም በእንቅስቃሴውም የአላህ **ፍጥረት** መሆኑን ማመን። አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ ٱللَّهُ خَٰلِقُ كُلِّ شَيۡءٖ ﴾

((አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው)) (ዙመር 62)

﴿ وَٱللَّهُ خَلَقَكُمۡ وَمَا تَعۡمَلُونَ ٩٦ ﴾

((አላህ እናንተንም የምትሰሩትንም ፈጠረ)) (ሳፋት 96)

(7). የላኢላህኢለላህ መሰረት (አርካን)

ለዚህች ታላቅ ቃል ሁለት መሰረቶች (አርካኖች) አሏት እነርሱም ነፍይ (ውድቅ ማድረግ) እና ኢስባት (ማፅደቅ) ናቸው።

1ኛው አርካን **ላኢላሃ** (አምላክ የለም) የሚለው ሲሆን ከአላህ ውጭ ካሉ ነገራቶች ሁሉ አምልኮትን ውድቅ ያደርጋል

ማጋራትን ያጣጥላል ከአላህ ውጭ በሚመለኩ ነገራቶች ሁሉ መካድን ግዴታ ያደርጋል።

2ኛው አርካን **ኢለላህ** (አላህ እንጂ) ይህ ደግሞ አምልኮትን ለአላህ ብቸኛ በማድረግ ያፀድቃል እንዲሁም በሁሉም የአምልኮ ዓይነቶች አላህን መነጠል እንደሚገባ ያመላክታል። ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ

ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴾

((በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ገመድ በእርግጥ ጨበጠ)) (በቀራ 256)

‹‹በጣዖትም የሚክድ›› የሚለው ንግግር ላኢላሃ የሚለውን 1ኛውን አርካን የሚተረጉም ሲሆን **‹‹በአላህ የሚያምን** የሚለው ደግሞ **ኢለላህ** ለሚለው ሁለተኛው አርካን ትርጉም ነው።

(8). የላኢላሃኢለላህ መስፈርቶች

የላኢላሃኢለላህ መስፈርቶች ስምንት ናቸው እነርሱም፡-

1.እውቀት ይህቺ ቃል የያዘችውን የማዕደቅና ውድቅ የማድረግ ትርጉምን ማወቅ

ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል

﴿ فَٱعۡلَمۡ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱللَّهُ ﴾

((ከአላህ ሌላ በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩንም እወቅ)) (መሀመድ 19)

በሌላም አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል

﴿ إِلَّا مَن شَهِدَ بِٱلۡحَقِّ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ٨٦ ﴾

‹‹በእውነት ከመሰከሩት በስተቀር›› **በላኢላሃኢለላህ ማለት ነው**

‹‹እነርሱ የሚውቁ ሆነው›› **ይህ ማለት በምላሶቻቸው የተናገሩትን በልቦቻቸው እስከሚያውቁት ማለት ነው።።**

የአላህ መልክተኛም(صلى الله عليه وسلم) እንዲህ ብለዋል

« مَنْ مَاتَ وَهُوَ يَعْلَمُ أَنَّهُ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ دَخَلَ الْجَنَّةَ»

((ከአላህ ሌላ በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን እያወቀ የሞተ ሰው ጀነት ገባ))

2. <u>እርግጠኝነት</u> የጥርጣሬ ተቃራኒ ሲሆን ስለዚህች ቃል ሙሉ እውቀት ሊኖረን ይገባል አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ ثُمَّ لَمْ
يَرْتَابُوا۟ وَجَٰهَدُوا۟ بِأَمْوَٰلِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ
أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلصَّٰدِقُونَ ﴿١٥﴾﴾

(((እውነተኞቹ) አማኞች እነዚያ በአላህና በመልክተኛው ያመኑት ከዚያም ልተጠራጠሩት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው በአላህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው:: እነዚያ አነርሱ እውነተኞቹ ናቸው::)) *(ሁጁራት 15)*

አላህ በዚህ አንቀፅ የሚነግረን አማኞች በአላህና በመልክተኛው የማመናቸው መስፈርት አለመጠራጠራቸው መሆኑን ነው:: ተጠራጣሪ የሆነ ሰው ግን የሚመደበው **ከሙናፊቆች** ነው:: እንዲሁም ሙስሊም በዘገበውና አቡ ሁረይራ ባስተላለፈው ሐዲስ የአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) እንዲህ ይላሉ

« أَشْهَدُ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَأَنِّى رَسُولُ اللَّهِ لاَ يَلْقَى اللَّهَ بِهِمَا عَبْدٌ غَيْرَ شَاكٍّ فِيهِمَا إِلاَّ دَخَلَ »الْجَنَّةَ

((ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለና እኔም የአላህ መልክተኛ መሆኔን እመሰክራለው እነዚህን ሁለት የምስካሬ ቃሎችን ሳይጠራጠር በመያዝ አላህን የሚገናኝ ማንም ሰው የለም ጀነት ቢገባ እንጂ።))

3. ኢኽላስ የሽርክ ተቃራኒ

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَلَا لِلَّهِ ٱلدِّينُ ٱلۡخَالِصُۚ ﴾

((ንቁ ፍፁም ጥሩ የሆነው ሀይማኖት የአላህ ብቻ ነው))
(አዝዙመር 3)

﴿ فَٱعۡبُدِ ٱللَّهَ مُخۡلِصٗا لَّهُ ٱلدِّينَ ٢ ﴾

((አላህንም ሐይማኖትን ለርሱ ብቻ ያጠራህ ሆነህ ተገዛው)) (አዝዙመር 2)

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ዒትባን ኢብኑ ማሊክ ባስተላለፈው ሐዲስ የአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) እንዲህ አሉ

إِنَّ اللَّهِ حَرَّمَ عَلَيْ النَّار أَنْ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ

((የአላህ ፊት ፈልጎ ላኢላሃኢላላህ ባለ ሰው ላይ አላህ እሳትን ሀራም አደርጓል))

4. እውነተኛነት(24 የሀሰተኛነት ተቃራኒ ሲሆን ከንፍቅና ይከላከላል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَحَسِبَ ٱلنَّاسُ أَن يُتْرَكُوٓاْ أَن يَقُولُوٓاْ ءَامَنَّا وَهُمْ لَا يُفْتَنُونَ ٢ وَلَقَدْ فَتَنَّا ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ ۖ فَلَيَعْلَمَنَّ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ صَدَقُواْ وَلَيَعْلَمَنَّ ٱلْكَٰذِبِينَ ٣ ﴾

(24) ይህ ማለት አንድ ሰው ይህችን ቃል ሲናገር ከልቡ እውነተኛ ሆኖ መሆን አለበት በምላሱ ብቻ ተናግሮ ልቡ የውሸቱን ከሆነ ይህ ሰው ሙናፊቅ ነው።

((ሰዎች አምነናል በማለታቸው ብቻ እነሱ ሳይፈተኑ የሚተው መሆናቸው ጠረጠሩን? እነዚያን ከነርሱ በፊት የነበሩትን በእርግጥ ፈትነናል እነዚያን እውነት የተናገሩትን አላህ በእርግጥ ያውቃል ውሸታሞችንም ያውቃል)) *(አል ዓንከቡት 2-3)*

በሌላም አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَقُولُ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَبِٱلْيَوْمِ ٱلْأَخِرِ وَمَا هُم بِمُؤْمِنِينَ ۝٨ يُخَٰدِعُونَ ٱللَّهَ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَمَا يَخْدَعُونَ إِلَّآ أَنفُسَهُمْ وَمَا يَشْعُرُونَ ۝٩ فِى قُلُوبِهِم مَّرَضٌ فَزَادَهُمُ ٱللَّهُ مَرَضًا ۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌۢ بِمَا كَانُواْ يَكْذِبُونَ ۝١٠ ﴾

((በአላህና በመጨረሻው ቀን አምነናል የሚሉ አሉ እነርሱ (እውነተኛ) አማኞች አይደሉም አላህንና እነዚያ ያመኑትን ያታልላሉ ነፍሶቻቸውን እንጂ አያታልሉም (ይህንን ግን) አያውቁም በልቦቻቸው ውስጥ (የንፍቅና) በሽታ አለባቸው አላህም በሽታን ጨመረባቸው ለነርሱም ይዋሹ በነበሩት ምክንያት አሳማሚ ቅጣት አላቸው።)) (አል በቀራ 8-10)

የአላህ መልክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

5. ውዴታ ይህቺን ቃል፣ እሷ ያመላከተችውንና የርሷን አራማጆች መውደድ እንዲሁም ለርሷ ብሎ መወዳጀትና ለርሷ ብሎ ጠላት መሆን

አላህ በተከበረው ቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَن يَرۡتَدَّ مِنكُمۡ عَن دِينِهِۦ فَسَوۡفَ يَأۡتِي ٱللَّهُ بِقَوۡمٖ

يُحِبُّهُمۡ وَيُحِبُّونَهُۥٓ

((እናንተ ያመናችሁ ሆይ ከናንተ ውስጥ ከሀይማኖቱ የሚመለስ አላህ (በናንተ ምትክ) የሚወዳቸውና የሚወዱትን ህዝቦች በእርግጥ ያመጣል ...)) (አል ማኢዳ 54)

የአላህ መልክተኛም(صلى الله عليه وسلم) እንዲህ ይላሉ

« ثَلاَثٌ مَنْ كُنَّ فِيهِ وَجَدَ بِهِنَّ حَلاَوَةَ الإِيمَانِ مَنْ

كَانَ اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَحَبَّ إِلَيْهِ مِمَّا سِوَاهُمَا وَأَنْ يُحِبَّ الْمَرْءَ لاَ يُحِبُّهُ إِلاَّ لِلَّهِ وَأَنْ يَكْرَهَ أَنْ يَعُودَ فِى الْكُفْرِ بَعْدَ أَنْ أَنْقَذَهُ اللَّهُ مِنْهُ كَمَا يَكْرَهُ أَنْ يُقْذَفَ فِى النَّارِ»

((ሶስት ባህሪያት ያሉት ሰው የኢማንን ጣዕም አጣጥሟል ለማንም ይበልጥ አላህና መልክተኛው ከርሱ ዘንድ ተወዳጅ መሆናቸው፤ አንድን ሰው ሲወድ ለአላህ ብሎ መሆኑና አላህ ከኩፍር ካዳነው በኋላ እንደገና ወደኩፍር መመለስን እሳት ውስጥ የመጨመርን ያህል ሲጠላ))

6. **መጎተት** በግልፅም ይሁን በድብቅ ለዚህች ቃልና ለምታመላክተው ጉዳይ ተጎታች (ታዛዥ) መሆን ይገባል ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَن يُسۡلِمۡ وَجۡهَهُۥٓ إِلَى ٱللَّهِ وَهُوَ مُحۡسِنٞ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰۗ وَإِلَى ٱللَّهِ عَٰقِبَةُ ٱلۡأُمُورِ ٢٢ ﴾

((እርሱ መልካም ሰሪ ሆኖ ፊቱን ወደ አላህ የሚሰጥ ሰው ጠንካራ ገመድን በእርግጥ ጨበጠ ::))
(ሉቅማን 22)

ይህ ጠንካራ ገመድ ‹‹**ላኢላሃኢላላህ**›› ነው

በሌላም የቁርኣን አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤۡمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيۡنَهُمۡ ثُمَّ

لَا يَجِدُواْ فِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَرَجٗا مِّمَّا قَضَيۡتَ وَيُسَلِّمُواْ تَسۡلِيمٗا ٦٥ ﴾

((በጌታህም እምላለው በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያሰፈርዱህ ከዚያም ***hፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍፁም መታዘዝን እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም (አማኝ አይሆኑም)))*** (ኒሳ 65)

7. መቀበል የመመለስ ተቃራኒ

ለዚህም ማስረጃ ይህቺን ቃል አልቀበልም ስላሉት የእሳት (የጀሀነም) ሰዎች ጉዳይ እንዲህ ይለናል፡-

﴿ إِنَّهُمۡ كَانُوٓاْ إِذَا قِيلَ لَهُمۡ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱللَّهُ يَسۡتَكۡبِرُونَ ٣٥ ﴾

﴿ وَيَقُولُونَ أَئِنَّا لَتَارِكُوٓاْ ءَالِهَتِنَا لِشَاعِرٖ مَّجۡنُونِۭ ﴾

((እነርሱ ከአላህ ሌላ በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበር እኛ ለእብድ ባለቅኔ ብለን አማልክቶቻችንን የምንተው ነን? ይሉም ነበር)) (ሳፉት 35 -36)

8. በጣዖት መካድ አንድ ሰው ከሽርክና ከክህደት እንዲሁም ከሚያራምዱትም ሰዎች እራሱን ማጥራት አለበት ካለበለዚያ እምነቱ (ኢማኑ) ትክክል አይሆንም። ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ

قل

بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَا وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴾ :

((በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው መበጠስ የሌለበትን ጠንካራ ገመድን በእርግጥ ጨበጠ)) (በቀራ 256)

እነዚህ ስምንት መስፈርቶች በዚህ ግጥም ተሰብስበዋል

علم يقين وإخلاص مع
محبة وانقياد والقبول لها
وزيد ثامنها الكفران منك
سوى الإله من الوثان قد

ትርጉሙ

እውቀት ውዴታና እውነተኛነት

<u>መቀበል</u> <u>መጎተት</u> <u>እርግጠኝነት</u>

<u>ኢኽላስ</u> ሰባተኛ ለአላህ ስራን ማጥራት

እንዲሁም <u>መካድ</u> ነው በሁሉም ጣዖታት

እነዚህ ስምንቱ መረጃ ያላቸው

የላኢላሃኢለላህ መስፈርቶቹ ናቸው

ወሳኝ ናቸውና በደንብ አፍሟቸው

(9). እስልምናን የሚያበላሹ ነገሮች

1. በአላህ አምልኮ ውስጥ ማጋራት (ሽርክ)

ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል

﴿ إِنَّهُۥ مَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدۡ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ ٱلۡجَنَّةَ وَمَأۡوَىٰهُ ٱلنَّارُ ﷺ

وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ أَنصَارٖ ٧٢ ﴾

((እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በሱ ላይ ጀነትን በእርግጥ እርም አደረገ መኖሪያውም እሳት ናት ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም)) (አል.ማኢዳ 72)

የሞቱ ሰዎችን መለመን እነርሱን እርዳታ መጠየቅ ለነርሱ ስለትን መሳልና እርድ ማረድ ከሽርክ ተግባራቶች ይመደባሉ።

2. በአላህና በእርሱ መካከል አማካይ (አማላጅ) በማድረግ እነዚህን ሰዎች የሚለምን ምልጃን የሚጠይቃቸው በእነርሱም የሚመካ የሆነ ሰው በእርግጥ ክዷል።

3. አይሁድና ነሳራ የመሰሉትን አጋሪዎችና ሙርተዶች ከሀዲ ናቸው ያላለ ወይንም ከሀዲ በመሆናቸው ላይ የተጠራጠረ ወይንም የነርሱን (ሀይማኖታዊ) አካሄድ ትክክል ነው ያለ በእርግጥ ክዷል።

4. ከአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) ቀና መንገድ ውጭ ያለ መንገድ ከርሳቸው መንገድ የተሻለ ሙሉ ነው ብሎ ያመነ ወይንም ከርሳቸው ፍርድ ውጭ ያለ ፍርድ ከርሳቸው የተሻለ ወይንም እኩል ነው ብሎ ያመነ፡- ይህ ማለት የጣኡትን ፍርድ ከርሳቸው ፍርድ እንደሚያስበልጡት ማለት ነው ይህ ሰው በእርግጥ ክዷል።

5. ቢተገብረውም እንኳን የአላህ መልክተኛ ይዘው ከመጡት (ሸሪዓ) አንዳች ነገር የጠላ በእርግጥ ክዷል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ كَرِهُواْ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ

فَأَحۡبَطَ أَعۡمَٰلَهُمۡ ٩ ﴾

((... ይህ እነርሱ አላህ ያወረደውን ስለጠሉ ነው ስለዚህ ሰራዎቻቸውን አበላሸባቸው።)) መሐመድ 9)

6. በአላህ ሃይማኖት ወይም በአላህ ፍርድ ማለትም በምንዳውም ይሁን በቅጣቱ እንዲሁም በረሱል ሱና ወይንም በሰሀቦች ላይ ያላገጠ አሊያም እነርሱን የሰደበ በእርግጥ ከሀዲ ሆኗል።

ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلْ أَبِاللَّهِ وَءَايَٰتِهِۦ وَرَسُولِهِۦ كُنتُمْ تَسْتَهْزِءُونَ ٦٥ لَا تَعْتَذِرُوا۟ قَدْ كَفَرْتُم بَعْدَ إِيمَٰنِكُمْ ﴾

((በአላህና በአንቀፆቹ በመልክተኛውም ታላግጡ ነበራችሁን? አታማኝኙ በላችው ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ክዳችኋል))

(አትዑባ 65-66)

7. ሺህርና ከዚሁ የሚመደቡትን <u>ሰርፍና አጥፍ</u> የሚባሉትን የሰራ ወይም የገዛ ወይም በነርሱ የተደሰተና የወደደ በእርግጥ ክዷል። ለዚህም ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَا يُعَلِّمَانِ مِنْ أَحَدٍ حَتَّىٰ يَقُولَآ إِنَّمَا نَحْنُ فِتْنَةٌ فَلَا

تَكْفُرْ ﷺ ﴾

((አኛ መፈተኛ ነን አትካድ እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም)) (አል በቀራ 102)

8. አጋሪያንንና ከሀዲያንን ለሀይማኖታቸው ብሎ መውደድ

እንዲሁም እነርሱን በሙስሊሞች ላይ መተባበርና መርዳት ለዚህ ማስረጃ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَن يَتَوَلَّهُم مِّنكُمْ فَإِنَّهُۥ مِنْهُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ

ٱلظَّٰلِمِينَ ٥١ ﴾

((ከናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱ ነው አላህ አመፀኞችን ህዝቦች አያቀናም)) (አልማኢዳ 51)

9. ኸድር ከነብዩ ሙሳ ሸሪዓ መውጣት እንደቻለው ሁሉ ከፊል ሰዎች ከነብዩ መሐመድ ሸሪዓ መውጣት ይችላሉ ብሎ ያመነ በእርግጥ ክዷል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ ٱلْإِسْلَٰمِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي

ٱلْءَاخِرَةِ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٨٥﴾ ﴾

ከኢስላም ሌላ ሀይማኖት የሚፈልግ ሰው ፈፅሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም እርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው)) (አል ኢምራን 85)

10. ከአላህ ሃይማኖት (ከእስልምና) ሙሉ በሙሉ ቸልተኛ መሆን ይህ ማለት አይማረውምም በርሱም አይሰራም አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّن ذُكِّرَ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِۦ ثُمَّ أَعْرَضَ عَنْهَآ ۚ إِنَّا مِنَ

ٱلْمُجْرِمِينَ مُنتَقِمُونَ ﴿٢٢﴾ ﴾

((በጌታውም አንቀፆች ከተገሰፀና ከዚያም ከተዋት ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም) እኛ ከተንከለኮቹ ተበቃዮች ነን)) (ሰጅዳ 22)

እነዚህን እስልምናን የሚያበላሹ ተግባራትን የፈፀመ ሰው (የተገደደ ሰው ካልሆነ በስተቀር) ለቀልድም ብሎ ይሁን ከምር እንዲሁም በፍርሀት የፈፀመ ሰው እኩል ነው (ዑዝር የለውም)።

(10). የተወሱል ክፍሎች

ተወሱል ለሁለት ይከፈላል

1. የሚፈቀድ ተወሱል
2. የሚከለከል ተወሱል

(11).ተፈቃጅ የሆኑት የተወሱል ዓይነቶች

ተፈቃጆቹ የተወሱል ዓይነቶች ሦስት ናቸው፡- እነርሱም፡-

1. በአላህ ስምና ባሪያቶች እንዲሁም በስራዎቹ ወደርሱ ተወሱል ማድረግ ለዚህ ማስረጃው አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلِلَّهِ ٱلْأَسْمَآءُ ٱلْحُسْنَىٰ فَٱدْعُوهُ ﴾

((ለአላህም መልካም ሰሞች አሉት (ስትፀልዩ) በርሱም ጥሩት)) (አል-አዕራፍ 180)

በሌላም አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል:-

﴿ وَأَدۡخِلۡنِي بِرَحۡمَتِكَ فِي عِبَادِكَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴾

((በቸርታህም በመልካሞቹ ባሮችህ ውስጥ አግባኝ)) (ነምል 19)

በተጨማሪም ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ካዕብ ኢብኑ ኡጅራ ባስተላለፈው ሐዲስ የአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) እንዲህ ብለዋል፡-

« قُولُوا اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ كَمَا صَلَّيْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ إِنَّك حَمِيدٌ مَجِيدٌ اللَّهُمَّ بَارِكْ عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ كَمَا بَارَكْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ ».

በሉ ((አላህ ሆይ በኢብራሒምና በቤተሰቦቻቸው ላይ ሰለዋት እንዳወረድክ ሁሉ በመሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይም ሰለዋት አድርግ አንተ ምስጉንና የተላቅህ ነህ። በኢብራሒምና በቤተሰቦቻቸው ላይ ረድዔትን እንዳወረድክ ሁሉ በመሐመድና

በሌተሰበቻቸው ላይ ረድዔት አስፍን። አንተ ምስጉንና የተላቅህ ነህ።))

2. በመልካም ስራ ወደ አላህ ተወሱል ማድረግ ለዚህ ማስረጃ አላህ በቁርኣን ያሰፈረው የአማኞች ዱዐ ነው፡-

﴿ٱلَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَآ إِنَّنَآ ءَامَنَّا فَٱغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَا

وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ١٦﴾

((ጌታችን ሆይ እኛ አመንን ሀጥያቶቻችንንም ማርልን የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን)) (አል ዒምራን 16)

በሌላም የቁርኣን አንቀፅ እንዲህ ይላል፡-

رَبَّنَآ ءَامَنَّا بِمَآ أَنزَلۡتَ وَٱتَّبَعۡنَا ٱلرَّسُولَ فَٱكۡتُبۡنَا مَعَ

ٱلشَّٰهِدِينَ ٥٣﴾

((ጌታችን ሆይ ባወረድከው አመንን መልክተኛውንም ተከተልን ከመስካሪዎችም ጋር መዝግበን)) (አል ዒምራን 53)

ለዚህኛው የተወሱል ዓይነት መረጃ ከሚሆኑት ሐዲሶች መካከል ቡኻሪና መስሊም የዘገቡትና አብደላ ኢብኑ ዑመር ያስተላፈው የሶስቱ ሰዎች ታሪክን የሚነግረን ሐዲስ ነው፡-

እነዚህ ሶስት ሰዎች መንገድን እየተጓዙ ሳለ ዝናብ ይመጣባቸዋል፤ ለመጠለልም ብለው ወደ አንድ ተራራ ላይ ወደሚገኝ ዋሻ ውስጥ ይገባሉ። ይሁንና እነርሱ እውስጥ ባሉበት ሁኔታ ከተራራ ላይ እየተንከባለለ የመጣ አንድ ትልቅ ቋጥኝ የዋሻውን በር ዘጋባቸው። መውጪያም አጡ። ይህ በእንዲህ እንዳለ እነዚህ ሶስት ሰዎች እርስበርሳቸው ‹‹እስቲ ከዚህ ቀደም ለአላህ ብላችሁ የሰራችሁትን መልካም ስራ አስታውሱ በዚህም ስራ ወደ አላህ በመቃረብ (ተወሱል በማድግ) ለምኑት አላህ ከዚህ ጭንቅ በዚህ ምክንያት ያወጣን ዘንድ እንከጅላለንና›› ተባባሉ። አንደኛው ለአላህ ብሎ ለወላጆቹ ያደረገውን መልካም ስራ በማስታወስ ወደ አላህ ተወሱል አደረገ (ተቃረበ)። ሁለተኛውም ዝሙትን ለመፈፀም ምቹ አጋጣሚን አግኝቶ አላህን በመፍራትና ጥብቅነትን በመምረጥ እንደተወ በማስታወስ በዚህ መልካም ተግባር ወደ አላህ ተቃረበ ሶስተኛው ደግሞ አደራን (አማናን) በመጠበቁ ይህንን መልካም ስራ በማስታወስ ወደ አላህ ተቃረበ በዚህም

ምክንያት አላህ ከጭንቁ ገላገላቸውና ከዋሻው በመውጣት መንገዳቸውን ቀጠሉ።።

3. በመልካም ሰው ዱዐ ወደ አላህ ተወሱል ማድረግ

ዑመር ኢብኑ አልኸጣብ በዐባስ ኢብኑ አብድል መጠለብ ዱዐ ተወሱል ያደርግ እንደነበረው ማለት ነው

(ኢማሙል ቡኻሪ 1010ኛው ሐዲስ ላይ ዘግቦታል)

4. በውሳጣችን ያለውን ወደ አላህ ፈላጊነትና ሐጃ ግልፅ በማድረግ ወደ አላህ መቃረብ (ተወሱል ማድረግ) ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው አላህ የነገረን የነብዩላህ አዩብ ዱዓ ነው።።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَيُّوبَ إِذْ نَادَىٰ رَبَّهُۥٓ أَنِّي مَسَّنِيَ ٱلضُّرُّ وَأَنتَ أَرْحَمُ

ٱلرَّٰحِمِينَ ﴿٨٣﴾ ﴾

((አዩብም ጌታውን እኔ መከራ አገኘኝ አንተም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ›› ሲል በተጣራ ጊዜ አስታውስ)) (አል- አምቢያ 83)

ስለ ነብዩላህ ዘከርያም እንዲህ ይላል፡-

﴿ قَالَ رَبِّ إِنِّي وَهَنَ ٱلۡعَظۡمُ مِنِّي وَٱشۡتَعَلَ ٱلرَّأۡسُ شَيۡبٗا وَلَمۡ

أَكُنۢ بِدُعَآئِكَ رَبِّ شَقِيّٗا ٤ ﴾

((ጌታዬ ሆይ እኔ አጥንቴ ደከመ ራሴም በሽበት ተንቀለቀለ አንተንም በመለመኔ ጌታዬ ሆይ (ምንጊዜም) እድል ቢስ አልሆንኩም አለ)) (መርየም 4)

(12) .ክልክል የሆኑት የተወሱል ዓይነቶች

ክልክል የሆነው ተወሱል ሁለት ዓይነት ነው፡- እነርሱም

1. ቢድዐ (መጤ) የሆነ ተወሱል፡- ለምሳሌ በነብያቶችና በሳሊሆች ክብር እንዲሁም በአካሎቻቸው ተውሱል ማድረግ

2. ሽርክ የሆነ ተወሱል፡- ይህ ደግሞ ሙሽሪኮች በጣዖቶቻቸው ተወሱል እንደሚያደርጉት ማለት ነው

(13). በነብያችን ተወሱል የማድረግ ፍርድ

በነብያችን(صلى الله عليه وسلم) ተወሱል ማድረግ በሶስት ይከፈላል፡-

1ኛው - በርሳቸው በማመን እርሳቸውን በመውደድና በመከተል ተወሱል ማድረግ፡- ይህ ዓይነቱ ተወሱል በህይወትም እያሉ ይሁን ከሞቱ በኋላ የሚፈቀድና የሚቻል ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ አላህ ስለ ኢማን ሰዎች ንግግር ሲነግረን እንዲህ ይላል፡-

﴿ رَّبَّنَآ إِنَّنَا سَمِعۡنَا مُنَادِيٗا يُنَادِي لِلۡإِيمَٰنِ أَنۡ ءَامِنُواْ بِرَبِّكُمۡ

فَـَٔامَنَّاۚ رَبَّنَا فَٱغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَا وَكَفِّرۡ عَنَّا سَيِّـَٔاتِنَا وَتَوَفَّنَا مَعَ

ٱلۡأَبۡرَارِ ﴿١٩٣﴾

((ጌታችን ሆይ እኛ በጌታችሁ እመኑ በማለት ወደ እምነት

የሚጠራንን ጠሪ ሰማንና አመንን

ጌታችን ሆይ ኃጥያቶቻችንን ማርልን ክፉ ስራዎቻችንንም

ከኛ ላይ አብስልን ከንፁዎቹም ሰዎች ጋር ግደለን))

(አል-ዒምራን 193)

2ኛው - በርሳቸው ዱዓ ተወሱል ማድረግ - ይህ ማለት ደሪርና ሌሎች ሶሀቦች የአላህ መልክተኛ ዘንድ እየመጡ ዱዓ አድርጉልን ይሏቸው እንደነበሩት ሲሆን ይህ ተግባር በህይወት እያሉ ችግር የሌለውና የሚፈቀድ ነበር ከሞቱ በኋላ ግን አይፈቀድም ምክንያቱም ዱዓ ማድረግ አይችሉም።

3ኛው - በክብራቸው ተወሱል ማድረግ ይህ ዓይነቱ ተወሱል በህይወትም እያሉ ይሁን ከሞቱ በኋላ ቢድዓ (መጤ) የሆነ የተከለከለ የተወሱል ዓይነት ነው ምክንያቱም የነብያችን ክብር

የራሳቸው ስራ ሳይሆን አላህ በችሮታው የለገሳቸው ነው ይህንን ክብር ደግሞ ራሳቸው እንጂ ማንም ሊጠቀምበት አይችልም።

(14). <u>የቀብር ዚያራ (ጉብኝት) ክፍሎች</u>

የቀብር ዚያራ ለሶስት ይከፈላል፡- እነሱም

1. **ሸሪዓዊ (የተፈቀደ) ዚያራ:**[25] - ይህ ዓይነቱ ዚያራ ዘያሪውን ሰው የሚጠቅም ነው ምክንያቱም ይገሰፅበታል ይመከርበታል ለሚቹም አላህ ወንጀሉን እንዲምረውና እንዲያዝንለት ዱዓ ስለሚያደርግ ሚቹም ተጠቃሚ ይሆናል

---

(25) የቀብር ዚያራ ሲባል ቀብርን ሄዶ መጎብኘት ሲሆን የአላህ መልክተኛ(صلى الله عليه وسلم) የመጎብኘትን ጥቅም አነስ ባወራው ሐዲስ እንዲህ ብለውናል፡-

((ቀብር መጎብኘትን ከልክያቸሁ ነበር ከአሁን በኋላ ጎብኟት ልብ ታረጥባለች ዓይንን ታስለቅሳለች አኼራን ታስታውሳለች(ነገር ግን) ውድቅ ንግግርን እንዳትናገሩ))።

ከውድቅ ንግግሮች ውስጥ ቀብር ውስጥ ያለውን ሚች መማፀን እርሱን እርዳታ መጠየቅና ሌሎች ሸሪዓችን የከለከላቸውን ንግግሮች መስራትን ያካትታል።

ነገር ግን መጥፎ ንግግርን መጠቀምም ይሁን ለዚህ ተብሎ ስንቅን በመጫን ረኸቦም ጉዞን ማድረግ አይቻልም።

2. **ቢድዓ (መጤ) የዚያራ ዓይነት**፦ የዚህ ዓይነቱ ዚያራ ከላይ በተራ ቁጥር አንድ ላይ ያለውን የሚፃረር ነው።

3. **ሽርክ ያለበት ዚያራ**፦ ይህ ዓይነቱ ዚያራ ደግሞ ዘያሪው ሰው በተለያዩ የሽርክ ዓይነቶች የሚዘፈቅበት ነው። ለምሳሌ ሚቶቹን (ቀብር ውስጥ ያሉትን) መማፀን ለነርሱ ማረድ ለነርሱ ስለትን ማድረስ እነርሱን እርዳታ መጠየቅ እነርሱን እገዛ መጠየቅ በነርሱ ጥበቃን መፈለግ...

(15). በረካን ከቦታዎች ወይም ከፋናዎች እንዲሁም ሙትም ይሁን ህያው ከሆኑ ሰዎች መፈለግ

ተበሩክ ማለት በረካን መፈለግ ማለት ነው በረካ ማለት ደግሞ አንድ መልካም ነገር በአምላካዊ ኃይል ባለበት ሁኔታ መቆየቱ ወይንም መጨመሩ ነው።

መልካምን ነገር ባለበት የሚያቆየውም ሆነ እንዲጨምር የሚያደርገው ይህንን የሚቆጣጠርና በርሱም ላይ ቻይ የሆነ አካል ሲሆን እርሱም አላህ ነው። እርሱ ነው በረካን የሚያወርድና የሚያፀናው። ፍጡር ግን በረካ መስጠትም

ይሁን ማስገንት እንዲሁም እንዲቆይና እንዲፀና የማድረግ አቅም የለውም።

በቦታዎች፣ በፋናዎች እንዲሁም ሙትም ይሁኑ ህያው በሆኑ ሰዎች በረካን መፈለግ አይፈቀድም። ምክንያቱም፦

1. ይህ ነገር በረካን ይሰጣል ተብሎ ከታመነ ሽርክ ነው
2. ይህንን ቦታ መዘየር (መጎብኘት) ወይም ከዚህ ቦታ ጋር መተሻሸትና መዳሰስ ከአላህ በረካን ያስገኛል ተብሎ ከታመነ ወደ ሽርክ የሚያዳርስ ተግባር ነው።

በደጋግ ሰዎች (በሳሊሆች) አካል ወይም በፋናዎቻቸው በረካን መፈለግ የማይፈቀድ ውድቅ ተግባር ነው። ምክንያቱም ከኛ በፊት ከነበሩት መልካም ሰዎች በአቡበክር ሲዲቅ ወይም በርሱ ላብ አሊያም በልብሱና በምራቁ በረካን ለመፈለግ ጥረት ያደርጉ ነበር ተብሎም ተሰምቶም አይታወቅም እንዲሁም በዑመርም በኡስማን በዓሊይ። እነዚህ ታላቅና ሳሊህ ሰዎች ከመሆናቸው ጋር በነርሱ በረካን ይገኛል ተብሎ አንድም ሰው ይህንን ተግባር ፈፅሞ አያውቅም።

ሰሀቦች በነብያችን (صلى الله عليه وسلم) አካል፣ ላብ፣ ምራቅ፣ ፀጉርና ልብሳቸው በረካ ይፈልጉ ነበር። ነገር ግን ይህ ተግባር በነብያችን ብቻ የተገደበ ነው ከዚህ ተቀይሶ በሌሎች ሳሊሆች

ይቅርና በአራቱ ኸሊፋዎችም ይሁን በአስሩ በህይወት እያሉ በጀነት በተበሰሩት ሰሀቦች እንኳን በረካ መፈለግ አይፈቀድም። ምክንያቱም ዒባዳ (አምልኮት) ነውና ዒባዳ ደግሞ ቁርአንና ሐዲስን በመከተል ብቻ የሚተገበር ነገር ነው። ልክ እንደዚሁ ደግሞ ሰሀቦች ነብያችን(صلى الله عليه وسلم) ከሞቱ በኋላ በቀብራቸውም ይሁን ይኖሩበት በነበረው ቤታቸው በረካን አይፈልጉም ነበር። እንዲሁም እርሳቸው በህይወት እያሉ የተቀመጡበትን ወይም የሰገዱበትን ቦታ እያሰቡ በረካን አይፈልጉም ነበር። ታዲያ ይህ እንዲህ ከሆነ በሌሎች ሳሊሆችና የአላህ ወዳጆች በፋናዎቻቸው በረካን መፈለግ ክልክልነቱ የበረታ ይሆናል።

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ አላህ ምስጋና የተገባው ነው